6 ትምህርት

ወደ እድገት የሚያደርሱ መሠረታዊ ነገሮች

እንድ የሕንጻ ሠራተኛ ያለ መሳሪያዎቹ ምን ማድረግ ይችላል? የሕንጻው ዕቅድ ምን ያህል ቆንጆ ቢሆንም፣ የሚዘራው ዘር የፈለገውን ያህል ምርጥ ቢሆንም፣ ሥራውን የሚያከናውንበት መሳሪያዎች ከሌሉት ምንም ሊያደርግ አይችልም። የእግኙ ዓላማና ግብ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ነው። ብዙ ጠቃሚ የሆኑ የእድገት መመሪያዎችንና የሚሰጠንና የሚቀሰቅሰን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በክርስቶስ ማደግ የበሰለ ሰው የሚቀበለውን መብትና ሃላፊነት ለመቀበልና ለመያዝ ያስችለናል። እንደ ልጅ ወዲህና ወዲያ እየተፍገመገምን እንዳንከራተት የሚጠብቀንና የሚረዳን በክርስቶስ ማደግ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለእነርሱ ያዘጋጀውን ትምህርት መቀበል የሚችሉት የበሰሉ ክርስቲያኖች ናቸው። ይህም ትምህርት ክርስቶስን ወደ መምሰልና ጠቃሚነት ወዳለው ዓላማና ግብ ይመራል። እያደገ ወይም እየበሰለ የሚሄደው ክርስቲያን በጌታ ዙፋን ፊት ስለሚጠብቀው የመጨረሻ ፈተና በሚገባ መገንዘብ ያስፈልገዋል።

እነዚህ ዓላማና ግቦች ላይ መድረስ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ እንደ እግዚአብሔር ታላቅ ሕንጻና ፍሬያማ የእርሻ መሬት መሆን ይዝናል። የጠነከረ የቤተሰብ ሃላፊነትም ሊገኝና ሊደረስበት የሚገባ ነው። እነዚህን ዓላማዎችና ግቦች የምናከናወነው እንዴት ነው? እነዚህን ነገሮች ለማከናወን ይህ ክፍለ ትምህርት በሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ እርምጃዎችን ይነግረናል። ከዚህ ቀጥሎ ያለውም የክፍለ ትምህርቱም አከፋፈል ወይም አስተዋፅኦ የሚያቀርብልን እግዚአብሔር ልጁን ወደ መምሰል ደረጃ እኛን ለማድረስ የሚቀምባቸውን መሳሪያዎች፣ የሰዎችን ድርጊቶችና ሁኔታዎች ነው።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት
- በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማደግ
- የጸሎት መንፈሳዊ ኃይል
- በክርስቶስ ስር አገልጋይ መሆንን ማወቅ
- የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት መረዳት
- ከመንፈስ ቅዱስ አመራር ጋር መተባበር
- ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሚኖረን ግንኙነት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- በእግኙ ውስጥ መንፈሳዊ እድገትን ለማዳበር አስፈላጊውን የሰው ምላሽ መግለጽ
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጸሎት መንፈሳዊ ባህሪይን ለማዳበር እንዴት እንደሚረዱ ማስረዳት
- መንፈስ ቅዱስና እግኙ በክርስቶስ እንዲያድግ እግኙን ለመርዳት እንዱ ባንዱ ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው ለይቶ ማወቅ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ስድስተኛውን ክፍለ ትምህርት በሚገባ አንብብ።
2. በክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ ላይ የተሰጡትን መልመጃዎች በጥንቃቄ ሥራ። እልፎ እልፎም መልሶችህን በመጽሐፉ ውስጥ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ።
3. ለመንፈሳዊ እድገት በጣም የሚረዱ መስለው የታዩህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር
4. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የሙከራ ፈተና ከወሰድክ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በጥንቃቄ አገናዝብ። በትክክል ያልመለስካቸውንም ጥያቄዎች አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

ራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት

ዓላማ 1 የኛ ስፍራ ከክርስቶስ ስፍራ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ።

እኛ እንደገና የተወለድነው በእግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ፣ ይህ ሊሆን የቻለው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን ስንቀበል ነው። እርሱ ስለ ኃጢአታችን የከፈለውን መሥዋዕት ስንቀበልና በኃጢአታችን በመጸጸት ከተመለስን በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን እንደሆነ በአፋችን ስንመሰክር ነው። ሮሜ 10:9-10 ስለዚሁ ሲገልጽ፦ "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ" ይላል።

አዲስ ኪዳን በመጀመሪያ በተፃፈበት በግሪክ ቋንቋ "ጌታ" ለሚለው ቃል የሚጠቀሙት 'ኩሪዎስ' በሚል ቃል ነው። በዚያን ዘመን በዚህ ቃል የሚጠቀሙት እንደ ሮማዊ ንጉሥ ለሆነ የከበረ ሰው ነበር። የሮሜ መልእክት በተጻፈበት ጊዜ እያንዳንዱ የሮማ ዜጋ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ መቅደሱ መሄድ ነበረበት። እዚያም እጣን ይቆነጥብና አሳት ውስጥ ጨምሮ በማጨስ፣ "ቄሳር ጌታ ነው! ቄሳር ጌታ ነው!" እያለ በጩኸት ድምጹን ያሰማ ነበር። "ኩሪዎስ" የሚለው ቃል "ፍጹም የሆነ" "ንጉሥና ገዢ" ማለት ነው። እይሁዶች ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ ቋንቋ በተረጎሙ ጊዜ "እግዚአብሔር" የሚል ትርጉም ያለው ቃል ፈለጉ። "ኩሪዎስ" የሚለውን ቃል መረጡና በብሉይ ኪዳን "ያሕዌ" በሚለው የዕብራይስጥ ቃል ፈንታ ተጠቀሙበት።

ለእንድ ክርስቲያን "ኢየሱስ ጌታ ነው" ብሎ መናገር እንዴት ያለ ትርጉም እንዳለው ትገነዘባለህ? ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ንጉሥ፣ ጌታና ገዢ ነው ማለት ነው። "ኢየሱስ ጌታ ነው" ስንል እንደ እቡነ ዘበሰማያት መደጋገማችን ሳይሆን፦ የሕይወቴ ጌታ ገዥና ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰየና ከፍተኛ ስፍራ ስላለው እርሱ የሕይወቴ ጌታ ነው ማለታችን ነው። እዚህ ላይ በቆላ 1:9-20 ላይ የተጻፈውን ቃል እንገብ። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ የሚያደርግ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመሆኑ "እርሱ ሁሉ ነገር ከመፈጠሩ በፊት የነበረ በኩር ልጅ እንደሆነና ሁሉ የተፈጠሩት በእርሱ እንደሆነ" ይነግረናል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረውም በእርሱና ለእርሱ እንደሆነም ይነግረናል።

(1). ቆላ 1:9-20ን በቁ. 18 ላይ ያለውን የመጨረሻውን ዐረፍተ ነገር በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፍ። ባነበብከው መሠረት ክርስቶስ የሚኖረው ምን ዓይነት ስፍራ ነው?

"የመጀመሪያ ስፍራ" ማለት የኔ ፍላጎቶች፣ ግንኙነቶችና ሕይወቴ ለርሱ ከምሰጠው ስፍራ ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ሲሆን ማለት ነው። ዓለምንና የግል ሕይወቴን የማይበት የእይን ብሌኔ ኢየሱስ ይሆናል። በቀላል መንገድ ክርስቶስ ያለማቋረጥ የሕይወቴ እዛኝና ተቆጣጣሪ ይሆናል ማለት ነው። ከእርሱ መመሪያን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለመቀበልና መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር የዘወትር ጸሎታችን ይህ ይሆናል። "እግዚአብሔር እምላካችን ሆይ፣ ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታችን ተቆጣጣሪ እንድናደርገው እርዳን። እርሱ አዳኛችን ስለሆነ በእርግጥ የሕይወታችን ጌታ ሊሆን ይገባዋል። ተገቢውን ተሳትፎ በማድረግ ለእርሱ ትእዛዝና ቁጥጥር ተገዢውን ምላሽ ለመስጠት እንድንችል ንቃትን ጨምርልን። በልባችን መንፈስ ቅዱስ እንዲኖርበትና ሌሎች ኢየሱስን በሕይወታችን ለማየት እንዲችሉ በየዕለቱ የመጀመሪያውን ስፍራ ለኢየሱስ መስጠት ማለት ምን እንደሆነ ስለ ስምህ ክብር ስትል አስተምረን" አሜን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጀመ

ዓላማ 2 መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ላይ ጋጢአት ከመሥራት እንዴት ሊጠብቀን እንደሚችል ለመግለጽ።

መንፈሳዊ እድገታችን የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ከምናሳልፈው ጊዜ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው የክርስቲያን የመማሪያ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያን የጦር መሣሪያና ካርታ እንዲሁም የመምሪያ መሳሪያ ከመሆኑም በላይ የዕለት ምግቡም ነው። ቃሉ መንፈስን ይጠብቃል፣ ብርሃን ይሰጣል፣ ሕይወትህን በእቅድ እንድትመራ ያደርግሃል። በ1ጴጥ 2:2 ላይ አዲስ ክርስቲያኖች አዲስ እንደተወለዱ ሕጻናት፣ ንጹህ የሆነውን የቃሉን ወተት መመኘት ይገባቸዋል። በዕብ 5:11-15 ላይ እንደሚነግረን ደግሞ ከሕጻንነት ወደ ብስለት የምንደርሰው በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ነው።

(2). ዕብ 4:12 እንብብ። ባነበብከው መሠረት የእግዚአብሔር ቃል የተመሳሰለው ከ _____ ጋር ሲሆን የሚፈርደውም _____ መርምሮ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል መንጻትን ወደ ሕይወታችን የሚያመጣበት መንገድ ስላለው ይህም ለመንፈሳዊ እድገታችን በጣም አስፈላጊ ነው።

(3). ዮሐ 15:1-4ን አንብብ። እዚህ ላይ ኢየሱስ በወይን ግንዱና በቅርንጫፉ የተጠቀመው በእርሱ ትምህርት ምክንያት ደቀ መዛሙርቱ ምን ለመሆን እንደሚችሉ ለመንገር ነው?

ሀ. ንጹሕ ለ. የበሰሉ ሐ. ጓደኞች መ. ክርስቲያኖች

መዝ. 119 ስለ እግዚአብሔር ቃል ምንነት የሚናገር በጣም አስገራሚ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ረጅሙ ምዕራፍ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ቁጥር ወይም ጥቅስ ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚናገርን ቃል የያዘ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የእርሱ ሕግ፣ የእርሱ ትእዛዝ፣ የእርሱ መመሪያ፣ የእርሱ ማስተማሪያ. . .ወዘተ ተብሎ ተገልጸአል። አሁን መላውን መዝ. 119 ለማንበብ ጥሩ አጋጣሚ ሲሆን፣ እንብበህ ስትጨርስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ግንዛቤህን ለማዳበር እንዲረዳህ ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች መልስ።

(4). በመዝ 119 ቁጥር 9 ላይ፦ "ንልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል?" የሚል ጥያቄ ያቀርባል። ሕይወታችንን ለማንጻት የምንችለው፦

ሀ. መጻሕፍት በማንበብ
ለ. ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ

ሐ. የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ

(5). *መዝ* 119:11 እንደገና ተመልከት። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ከመሥራት እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

በቀላሉ እንጋገር የእግዚአብሔር ቃል ከኃጢአት ይጠብቀናል ወይም ኃጢአት ከእግዚአብሔር ቃል ይጠብቀናል። የእርሱ ቃል ለሕይወታችን መመሪያም ይሰጠናል።

(6). በመዝ 119:105 ላይ የተጻፈውን ቃል በመጠቀም ባዶ ቦታውን ሙላ። ሕግህ ለእግሬ_____ ለመንገዴም _____ ነው።

(7). በመዝ 119:130 ላይ የተጻፈውን ቃል በመጠቀም የጎደለውን ቃል ሙላ። የቃልህ ፍቺ _____ ሕጻናትን _____ያደርጋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሊጠና የሚችልበት ብዙ መንገዶች አሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በየዕለቱ በማንበብ ያጠናሉ። አንድ "2-2-1" ተብሎ የሚጠራና ጠቃሚ ነው ተብሎ የቀረበ የአጠናን ዘዴ አለ። ይህ የአጠናን ዘዴ ከዘፍጥረትና ከማቴዎስ ወንጌል በመጀመር ሁለት ምዕራፍ ከብሉይ ኪዳን ሁለት ምዕራፍ ከአዲስ ኪዳን ማንበብ ሲሆን፣ በተጨማሪም አንድ ምዕራፍ ከመዝሙረ ዳዊት ወይም ከመጽሐፈ ምሳሌ በየዕለቱ ማንበብ ነው። ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ "ርዕሳዊ የአጠናን ዘዴ" ተብሎ የሚጠራው ነው። ይህ ዘዴ እንደ መንፈስ ቅዱስ ያለ ርዕስ ወስዶ በመጠቀም በዚሁ ርዕስ ስር ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እያስባሰቡ ጥናቱን ማካሄድ ነው።

ለመንፈሳዊ እድገታችን ቃሉን ማጥናት ወሳኝ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። እግዚአብሔር ሕያው ቃል የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚገልጠው በተጻፈው ቃል ዘኩል ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን የምንሄደው ቃሉን ለማጥናትና ለቃሉ ለመታዘዝ ለእግዚአብሔር በምንሰጠው ጊዜ መጠን ነው።

የጴሎሞች መንፈሳዊ ኃይል

ዓላማ 3 በሐዋ. 4:24-31 የአማኞች የጸሎት ሙጤት ምን እንደሆነ ለማግለጽ።

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። ከንጉሥ ጋር መነጋገር ለአማኙ ትልቅ መብትና እድል ነው። አማኙ ወደ መንፈሳዊ እድገት የሚመጣበት ኃይለኛ መንገድ ነው። በጸሎት ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን በይበልጥ እርሱን እየመሰልን እንድናደግ ይረዳናል።

አማኙ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ በተፃፈበት ቋንቋ "ጸሎት" ተብለው የተተረጎሙ አሥራ ስባት ቃላቶች አሉ። ከነዚህም ቃላቶች እያንዳንዱ የመጠየቅን ትርጉም በግልጽ ያዘሉ ናቸው። "ጸሎት" በተሻለ መንገድ ሊብራራ የሚችለው ከወላጆቹ ጋር በሚነጋገር ልጅ ነው። ልጁ እያደገ ሲሄድ የንግግሩ ደረጃም ከፍ እያለና እያደገ ይሄዳል። በጸሎት ርዕስ ላይ ራሱን የቻለ ሙሉ መጽሐፍ ለማውጣት ቢቻልም፣ በዚህ ክፍለ ትምህርት የምናተኩረው ግን ዘላቂነት ባለው በግል የጸሎት ሕይወት ላይ ነው።

(8). በዕብ 11:6 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ጥያቄዎቹን መልስ።

ሀ. ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ ምን ሊኖረን ይገባል?

ለ. እግዚአብሔር ሽልማት የሚሰጠው ለማን ነው?

ሰው በጸሎት ከእርሱ ጋር ለመገናኘት እንደሚችል እግዚአብሔር ወስኖአል። ጸሎት የተቀደሰ መብትና ታላቅ ኃላፊነት ነው። በራሳችን ሕይወትና በሌሎች ሕይወት ላይ ልዩነትና ለውጥ የሚያስገኘው ጸሎታችን መሆኑን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው።

(9). ለመንፈሳዊ እድገት የሚሆን በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ሁለት ገጾች በመለየት "የጸሎት ተስፋዎች" የሚል ርዕስ ስጣቸው። ለአሁኑ ከዚህ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ፣ የተሰጡትን ተስፋዎች ለመጻፍ እንዲያመችህ በመካከላቸው ስፍራ በመተው የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጻፍ።

ለጸሎት የተሰጡ ተስፋዎች

ኤፌ	1:7፤ 2:18፤ 3:12፤ 3:20፤ 6:11፤ 6:18
ዕብ	4:16፤ 7:25፤ 10:9፤ 10:19-20፤ 11:6
ዮሐ	9:31፤ 14:13፤ 14:14፤ 15:7 15:16፤ 6:24፤ 17:1-26
ሮሜ	5:8፤ 8:26፤ 12:12
1ጴጥ	3:7፤ 4:7፤ 5:7
ፊልጵ	4:6፤ 4:7፤ 4:19
መዝ	3:4፤ 5:3፤ 62:8

ስለ ጸሎት፣ ስለ እምነትና ስለ ጸሎት መልሶች የሚናገሩ ገና ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ከነዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዳንዶቹ መንፈሳችንን የሚያበረታቱና የጸሎት መሳሪያዎች ለመንፈሳዊ እድገታችን እንዴት አስፈላጊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ምሳሌ የሚሰጡንና የሚያስተምሩን ናቸው።

(10). በሐዋ 4:24-31 ላይ የተጻፈውን ጸሎት ካነበብክ በኋላ ጥያቄዎቹን መልስ።

ሀ. ደብን ጸሎት የጸለየው ማን ነው?
ለ. የዚህ ጸሎት ውጤቶች ምን ነበሩ?

በ18ኛው ክፍለ ዘመን ጆርጅ ሙለር የተባሉ ታላቅ መንፈሳዊ ሰው በሺህ የሚቆጠሩ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ይንከባከቡ ነበር። ቢሆንም ማንንም ሰው እርዳታ ፈጽሞ ጠይቀው አያውቁም። ለችግራቸው ሲጸልዩ ለሥራው የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ይሟላ ነበር። እኚህ ታላቅ የእምነትና የጸሎት ሰው የተነነዘቡት ነገር ቢኖር ቀኑን በጸሎት ለመጀመር ከመሞከር ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ቀኑን መጀመሩ የተሻለ እንደሆነ ነበር። ራስን ዝቅ እድርን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ማስላሰል እምነትንና ኃይልን እንደዚሁም የመጸለይ ፍላጎትን ያሰገኛል።

እንድ የቆየ የክርስቲያን መመሪያ "ጸሎት ነገሮችን ይለውጣል" ይላል። ጸሎት የሚለውጠው ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም ደግሞ እንደሚለውጥ መዘንጋት የለብንም። እግዚአብሔር እንዲጠቀምብን ከፈለግን የጸሎትን ትምህርት በሚገባ መማር ይኖርብናል። የፀሎት ትምህርት ከጥናት ይልቅ በይበልጥ በተግባር የምንማረው ትምህርት ነው። መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ ያስተምረናል። ስለ ጸሎት ምን ያህል ብዙ ወይም ምን ያህል ትንሽ እንደምታውቅ እይጭነቅህ። ሳታቋርጥ መጸለይህን ግን ጀምር፥ ከዚያም ይህንኑ ማድረግን ዘወትር ቀጥል።

(11). ዳን 6:10 አንብብ። የዳንኤል የጸሎት ሕይወት ዘለቄታ እንዴት ነበር?

በማንኛውም ስፍራ፥ በማንኛውም ጊዜ መጸለይ ይቻላል። በሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለን መጸለይ እንችላለን። ቢሆንም ጌታና እኛ በሕብረት የምንሆንበትን ጊዜ መወሰኑ አስፈላጊ ነው። መንፈሳችን ሊነቃቃና ብርቱ ልንሆን የምንችለው እንደዚሁም ለፅለቱ የሚሆን መመሪያ ሊለጠን የሚችለው በዚህ መንገድ ነው። ትንሽ ጸሎት ከትንሽ ኃይል ጋር እኩል ሲሆን፣ የበለጠ ጸሎት ከበለጠ ኃይል ጋር ብዙ ጸሎት ደግሞ ከብዙ ኃይል ጋር እኩል ይሆናል።

በክርስቶስ ስር አገልጋይ መሆንን ማመቅ

ዓላማ 4 በቆላ 1:10 ላይ የተጻፈውን ቃል በመጠቀም የአማኙን ሕይወትና አድራጎት ለመግለጽ።

ዘላቂነት ያለው የክርስትና ኑሮ የክርስቶስ የፍቅሩ አገልጋዮች እንደሆንን ማወቅን የሚጠይቅ ነው። "ዘላቂ" የሚለው ቃል "ስምምነትን" "መተባበርን" የሚያመለክት በመሆኑ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነ ቃል ነው። ከምናምነው ነገር ጋር እስካልተስማማን ድረስ ባህሪያችን ዘለቄታ ያለው ሊሆን አይችልም። በቀላል አነጋገር "እኛ የምናስተምረውን በሥራ መተርጎም ይገባናል።" በአፋችን የምንናገረውን እምነት በሕይወታችን ማረጋገጥ ያስፈልገናል።

(12). ቆላ 1:9-14ን አንብብ። በቁ. 10 ላይ በሰፈረው ቃል መሠረት አማኙ መኖር ያለበት እንዴት ነው? ዘወትርስ ምን ያደርጋል?

በቆላ 1:10 ላይ፦ "ዘወትር እርሱን ደስ የሚያሰኘውን እድርጉ" የሚለው ሐረግ ጌታ ልታደርጉ የሚፈልግባችሁን ነገር ሳያዛችሁ በፊት ማድረግን አጥብቆ የሚገልጽ ነው። ማንኛውም አገልጋይ የታዘዘውን ነገር ያደርጋል። ነገር ግን አፍቃሪ አገልጋይ ወይም አማኝ ግን የሚኖረው ለየት ባለ መንገድ ነው። ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ይመለከትና ከመታዘዙ በፊት እንኳ የሚያደርግ ነው። እርሱ፦ "ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታዬ ነው" ብሎ ሲናገር ከልቡ እንደሆነ ሕይወቱ ያመለክታል።

(13). 1ዜና 11:15-19 ላይ ስለ ሶስቱ የዳዊት ጀግኖች የተጻፈ አስገራሚ ታሪክ አለ። ታሪኩን ካነበብክ በኋላ ከጌታ ጋር በሚገባ ስለ መመላለስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አንድ አንቀጽ ጸፍ። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ታሪክ ባንተ ሕይወትም ተግባራዊ ያደርገዋል።

አቦን ደግሞ ቆላስያስ ምዕራፍ ሦስትን አንብብ። ብቻህን ከሆንክ ድምዕህን ከፍ አድርገህ አንብበው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ክርስቲያን እንዴት መመላለስ እንዳለበት የሚገልጽ ምሳሌ ነው። ኢየሱስን መምሰል ማለት የእርሱን ሃሳብና ዝንባሌ መከተል እንደሆነ ከፊልጵ 2:5-8 ላይ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ይህም ማለት ከአስገራሚው ጌታችን ጋር የአገልጋይ ግንኙነታችንን መቀበል ማለት ነው። ይህን ግንኙነት መቀበላችን የተመሠረተው በክርስቶስ ስር የእኛን አገልጋይነት ክልብ በመገንዘብ ነው። ይህም ግንዛቤ የሚያስገኘው አስደሳች የሆኑ ክርስቲያናዊ በረከቶችን ብቻ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ተግባሮችን የሚፈጽሙ መንፈሳዊ እድገትንም ደግሞ ያስገኛል። ኢየሱስ በእርግጥ ጌታችን ከሆነ ተግባሮቻችንን በተሟላ መጠን በደስታ እናከናውናለን።

በቅድስና መኖር

ዓላማ 5 ንቢአት የአንድን አማኝ መንፈሳዊ እድገት እንዴት አድርጎ እንደሚያሳይው ለማመልከት።

ዘለቂታ ያለው መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖር ሌላው መንገድ በቅድስና መኖር ነው። ይህ የእግዚአብሔርን ልዩ ቅድስና ስለሚያመለክት በጣም ጠቃሚ ነው። በሮሜ 6 ላይ ስለ ቅድስና የሚናገር ሲሆን ምዕራፉ ያዘለው ፍሬ ሃሳብ፦ "እግዚአብሔር በአጋውና በምሕረቱ ካዳነን በኃጢአት መንገዳችን መቀጠል የለብንም" የሚል ነው። ለቀድሞው የኃጢአት ምኞታችን እንደሞተ ሰዎች ሆነን መኖር እንዳለብንና በአዲሱ ሕይወታችን ለክርስቶስ መኖር እንዳለብን ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተምረናል።

(14). ሮሜ 6፡11-13 በጥንቃቄ አንብብ። ቁ. 11 እና 13 ለኃጢአት ስለ መሞትና በክርስቶስ ስለሚገኝ ሕይወት ይናገራል። ዘቁ. 13 ላይ በተጻፈው መሠረት ለአንድ የተለየ ዓላማ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ማስረከብ አለብን። ይህ ዓላማ የሚለየው እንዴት ነው?

በቅድስና ለመኖር አንደኛው መንገድ በሕይወታችን ለኃጢአት መኖር ስንጀምር ቶሎ ተሰምቶን ስንናዘዝ ነው። አንድ ክርስቲያን ኃጢአት ሲያደርግ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ኃጢአቱ ሊወቅሰው ዘወትር ታማኝ ቢሆንም ክርስቲያኖች ለዚያ የሚሰጡት ምላሽ ግን የተለያየ ነው። በክርስቲያኑና በእግዚአብሔር መካከል አንድ ነገር ከገባ ሰመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ እንደሚገባው ምላሽ እንዳይሰጥ ያደርገዋል። ብዙ ጊዜ "ዛሬ ዐሐይ አልወጣችም" እንላለን። ቢሆንም ዐሐይ ዘወትር እንደምትወጣ እናውቃለን። ይህ የሚሆነው በዐሐይና በእኛ መካከል አንድ የሚጋርድ ነገር ሲመጣ ነው። ደመና ይመጣና የዐሐይን ጨረር ከእኛ ያግደዋል።

ስለ ኃጢአት በመውቀስ ረገድ መንፈስ ቅዱስ ዘወትር ታማኝ ነው። እኛ ግን አንዳንድ ጊዜ የወቀሳውን ጨረር ለመሸፈን በትዕቢት፣ በእኔነት፣ በምክንያት ቸል እንላለን። ለመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ ራሳችንን ዝቅ በማድረግ ምላሽ ለመስጠት ብንመርጥ በ1ዮሐ 1፡7 ላይና 1፡9 ላይ አስገራሚ የሆኑ ሁለት ተስፋዎች ተስጥተውናል።

(15). በ1ዮሐ 1፡7 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ከኃጢአት ሁሉ የሚያነጻው

ሀ. የእግዚአብሔር ቃል ሐ. ብርሃን
ለ. የኢየሱስ ክርስቶስ ደም

(16). 1ዮሐ 1፡9 ላይ እኛ ማድረግ የሚገባን አንድ ነገር ምንድነው? እግዚአብሔርስ ስለ ኃጢአት የሚያደርጋቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ኃጢአት፣ በክርስቶስ ካለው ዕድገት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? *የመንፈሳዊ እድገት መንገዱን በመዝጋት* እድገቱን ያግደዋል፡ በክርስትና ሕይወታችን ዘላቂዎች ለመሆን፣ የምናስተምረውን በሥራ የምንተረጉም ሰዎች ለመሆን፣ ከኃጢአት መንጻትና ሕይወታችንን ከኃጢአት ነፃ ማድረግ ይኖርብናል። ለመንፈሳዊ እድገት የቅድስና ሕይወት አስፈላጊ ነው።

በፈቃድ መኖር

ዓላማ 6 በክርስቶስ ለማደግ ፈቃዳችንን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እን ዴት እንደምናዛምድ ለመግለጽ።

በእርግጥ ዘላቂነት ያለው የክርስትና ሕይወት አብዛኛውን ጊዜ የሚመሠረተው በእኛ ፈቃድ ላይ ነው። እኛ ማድረግ የሚገባንን ነገር እግዚአብሔር እያደርግልንም። የሰው ፈቃድ ከፍተኛው የመንፈሳችን ሰውታ በመሆኑ፣ ያዘልጥ እግዚአብሔርን የምንመሰልበት ሰፍራ ነው። አያንዳንዱ ክርስቲያን "እፈቅዳለሁ" የሚል እርግጠኛ የሆነ ፈቃድ ሲኖረው በአንጻሩ ደግሞ እርግጠኛ የሆነ "አልፈቅድም" የሚል ፈቃድ አለው። ውሳኔአችንን ለመደገፍ እግዚአብሔር እርዳታውንና ኃይሉን ለመሰጠት ተስፋ ስጥቶናል።

(17). በሚከተሉት በእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የለው ፈቃድ ከሰው ድርጊት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ግለጽ። ለምሳሌ ያህል የመጀመሪያው መልስ ተመልከት።

ሀ. ዳን 1፡8 ዳንኤል መርከሰን አልፈለገም።
ለ. ዳን 3፡18 _____
ሐ. ሉቃ 15፡18 _____
መ. አስ 4፡16 _____

ፊልጵ 2፡12-13 ላይ፡- "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" ይላል። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያሳዩን እርሱ ለእኛ ያለውን ፈቃድ ለማከናወን በእኛ ድርሻና በእግዚአብሔር ድርሻ መካከል ያለውን ትብብር ነው። እግዚአብሔር ሕይወታችን ዘለቄታ ያለው እድገት እንዲኖረው ስለሚፈልግ ዓላማውን ወደ ግቡ ለማምጣት ሊረዳን ፈቃደኛ ነው። *እኛም የራሳችንን ፈቃድ ለእርሱ ፈቃድ በማስገዛት መንፈሳዊ እድገትን እንለማመዳለን።*

(18). ስለ መንፈሳዊ እድገት የሚናገረው ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በቆላ 3፡17 ላይ የተጻፈው ነው። በዚህ ጥቅስ መሠረት በጌታ ኢየሱስ ስም ማድረግ የሚገባን ምንድን ነው?

ሀ. የምናደርገውንና የምንናገረውን ሁሉ
ለ. አብዛኛውን የምናደርገውንና የምንናገረውን
ሐ. መንፈሳዊ የሆኑትን ነገሮች ብቻ

የመማሪያ ቅጂችን አግልግሎት መረጃ

ዓላማ 7 የአማኙን መንፈሳዊ እድገት ከመንፈስ ቅዱስ የእውነት አገልግሎት ጋር ለማዛመድ።

የሰው ዋነኛው ክፍል መንፈስ በመሆኑ ክርስቲያናዊ እድገትም መንፈሳዊ ነው። የለው መንፈስ ከፍተኛው የለው ተፈጥሮ በመሆኑ አእምሮውን፣

ፈቃዱንና እግዚአብሔርን ማወቅን የሚያጠቃልል ነው። የእግዚአብሔርን መልክ ወይም አምሳያ በሰው የምናገኘው በመንፈሱ ነው።

(19). ዮሐ 4:24 ላይ የተጻፈው ቃል እንደሚያመለክተው እግዚአብሔር፦

ሀ. እንደሰው እንደሆነ ነው።
ለ. መንፈስ እንደሆነ ነው።
ሐ. ዘላለማዊ እንደሆነ ነው።
መ. ቸር እንደሆነ ነው።

ሰውና እግዚአብሔር የሚመሳሰሉት ሁለቱም የሚያስቡና አካል ያላቸው በመሆናቸው ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው። ውስጠኛው ሰውም መንፈስ ነው። ስለዚህ በቀላሉ ሊገናኙና ሕብረት ሊኖራቸው ይችላል። ሰው እግዚአብሔርን ሊያመልክ የሚችለው በመንፈስና በእውነት ነው። በኒፍለ ትምህርት 4 ላይ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ስለሚኖረው የአገልግሎት ድርሻ በመጠኑ ተመልክተናል፡ በዮሐ 16:7-15 ላይ እርሱ ቢሄድ መልካም እንደሆነ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው ጊዜ ነገሩ በጣም ቢያናውጣቸውም የእርሱ መሄድ አስፈላጊ የሆነው መንፈስ ቅዱስን ለመላክ ነበር።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አማኞች ማደግ የነበረባቸው በሚታየው በኢየሱስ አነሳሽነት ሳይሆን በማይታየው በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ነበር። ለዚህም እምነት አስፈላጊ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ሰውን ስለ ኃጢአቱ ይወቅሳል፣የደኅንነትን መንገድ ያሳያል፣ በነርሱዮስ አካል ወይም በቤተ ክርስቲያን ያስተምሳል፣ መንፈሳዊ እውነትን በማስተማር ለአገልግሎት ኃይል ይሰጣል። ስነርስትና ሕይወት የኃይል ምንጭ የሚሆነው እርሱ ነው። እርሱ ሊገሰጥና ሊከበር የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። አማኙም ወደ መንፈሳዊ እድገት ሊያርስ የሚችለው በዚሁ መንፈስ ነው። በዮሐ 16:8 ላይ የተጻፈው ቃል እንደሚነግረን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ሰዎችን ያስረዳል።

(20). በዮሐ 16:13 ላይ መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ የሚሰጠው ሁለት አገልግሎቶች ምንድን ናቸው?

ከላይ ለተጠቀሰው ጥያቄ የመጀመሪያው ነፍስ መልስ መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ እየመራ እንደሚያገለግል የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው ነፍስ ደግሞ እውነትን በመቀበልና በመታዘዝ በተግባር እንዲተረጉም አማኙን እንደሚረዳ የሚናገር ነው። እውነትን በተግባር ላይ ከማዋላችን በፊት አስቀድመን እውነትን ማወቅ ይኖርብናል። ልምምዳ እውቀቱ ላይ የሚጨመረው መንፈሳዊ እድገትን ለማዳበር ነው።

(21). በሐዋ 1:8 ላይ ስለ ሌላ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ያስተምረናል። ይህም አገልግሎት፦

ሀ. ኃጢአትን በአሳት ማጥፋት
ለ. ለአምልኮ ማዘጋጀት
ሐ. ለምስክርነት ኃይል መስጠት

ከመንፈስ ቅዱስ አመራር ጋር መተባበር

ዓላማ 8 የአማኙን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መተባበር በመግለጽ ከመንፈሳዊ እድገት ጋር ለማዛመድ።

ስለ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በመጠኑ ከተመለከትን አሁን ደግሞ ያምንመለከተው በኤፌ 5:18 ላይ የተጻፈውን ሲሆን፣ ቃሉም ሲናገር፦ "ወደ ጥፋት የሚመራችሁ ስለሆነ በወይን ጠጅ አትስከሩ፣ ይልቅስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ" የሚል ሃሳብ ያዘለ ነው። እዚህ ላይ "መሞላት" የሚለው ቃል ጠርመሙስን በውኃ እንደ መመሙላት ወይም ባዶ ቅርጫትን በፍራፍሬ እንደመመሙላት እንደ ማለት አይደለም። "የመሙላትን ወይም የመረከብን" ሃሳብ የሚያቀርብ የግሪክ ቃል ነው። መንፈስ ቅዱስ ባዶ የእቃ መያዣን እንደሚሞላ ንጥረ ነገር አይደለም። እርሱ ስብዕና ያለው፣ ሌላውን አካል ማለትም አማኙን ለመቆጣጠር ሕልውና ያለው አምላክ ነው።

በኤፌ 5:18 ላይ "መሞላት" የሚለው የግሪክ ቃል የሚያመለክተው *ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚገኝን ልምምድን* ነው። "መሞላታችን" መቀጠል አለበት ወይም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን አለብን። በሚነኛውም ነገር እንሞላ በዚያ ነገር ቁጥጥር ስር ሆንን ማለት ነው። ይህም አገላለጽ በፍቅር መሞላትን፣ በጥላቻ መሞላትን፣ በፍላጎት መሞላትን የሚያስይ ነው። የተፈጥሮ ባሕሪያችን በሚቆጣጠረን ጊዜ አንዳንድ ክፉ ድርጊቶች ጎልተው ይታያሉ። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ ግን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ይሆናል።

ገላ. 5:16-17 ላይ ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጋር የመተባበርን አስፈላጊነት አጥብቆ ይናገራል። ቃሉም፦ "በመንፈስ ኑሩ፣ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙ፣ ምክንያቱም የሥጋ ምኞት ከመንፈስ ምኞት ጋር ተቃራኒ ነው፣ የመንፈስ ምኞትም ከሥጋ ምኞት ጋር ተቃራኒ ነው የሚል ፍሬ ነገር ያዘለ ነው።"

(22). መለኮታዊ ባሕርይ እንዲቆጣጠረን ከፈቀድን በሕይወታችን ስለ ምንጠብቀው ፍሬ በአጭሩ ግለጽ (ገላ 5:22-23)።

የእግዚአብሔር መንፈስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ቢኖርም እያንዳንዱ አማኝ ለእርሱ መሪነት ራሱን አሳልፎ በመስጠት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መተባበር ይገባዋል። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መንፈስ ካስገዛን፣ ከእርሱ እየተማርን፣ ኃይልና ብርታትን ከእርሱ እያገኘን የመንፈሳዊ እድገታችንን ዓላማ እያጠናከርን እንሄዳለን።

በጋራ መረዳዳትና ማደግ

ዓላማ 9 እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ለምን እንዳኖረ ለመግለጽ።

አንድ አማኝ ብቻውን ሊያድግ አይችልም። በቤተሰብ ውስጥ እንደሚያድግ ልጅ፣ ክርስቲያኑም ለማደግ የሌሎች እርዳታ፣ የሌሎች ሕብረትና ድጋፍ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር የፈጠረን ከእርሱ ጋርና እርስ በርሳችን ሕብረትን እንድንፈልግ አድርጎ ነው።

(23). ዕብ 10:24-25 ላይ የተጻፈው ስለ አማኞች ሕብረት ትእዛዝ የሚሰጥ ነው። በቁ. 25 ላይ እንደተጻፈው መተው የሌለብን ልማድ፡

ሀ. መሰብሰባችንን ለ. ጸሎትን ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ንባብን

በአካባቢያችን የብዙ አማኞች መኖር ደስ የሚያሰኝ ነው። የክርስቲያኖች በአንድ ላይ መሰብሰብ ብዙ ጊዜ በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው። ይህ ምናልባት አንተ በምትኖርበት አካባቢ የማይቻል ይሆናል። ለጥቂት አማኞች ስብሰባ እንኳ ጌታችን በማቴ 18:20 ላይ የሚያበረታታ ተስፋ ሲሰጥ፡- ሁለትም ሆነ ሦስት በስሜ በተሰበሰቡበት በዚያ እገኛለሁ በማለት ተናግሮአል። ከእንድ ሌላ አማኝ ጋር መገናኘት እንኳ መንፈሳዊ ሕይወታችንን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ አስተዋዕዖ አለው። ሁለት አማኞች አብረው በመጸለይ አብረው ሲያገለግሉ ውጤታማነታቸውን እያበዙ ይሄዳሉ። (ዘዳ 32:30ና ዘሌ 26:8 ላይ የተጻፈውን ተመልከት)። ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን እንዲያሰራጩ ደቀ መዛሙርቱን የላካቸው በተለየ መንገድ ነበር።

(24). ሉቃ 10:1ን አንብብ። የመጀመሪያዎቹ የወንጌል ሰባኪዎች የተላኩት እንዴት እንደሆነ ግለጽ።

ለእግዚአብሔር ከሌሎች ጋር በጋራ የመሥራትን መሠረተ ሃሳብ በተመለከተ ማብራሪያ የሚሰጡ ሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። የሐዋ 10:23፤ 11:12 እና 15:36-41 ተመልከት። በቀደሙት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለአገልግሎት በመለየትና እንዲመሠከሩ በላከበት ጊዜ፣ ሁለት ሁለት፣ ሦስትና አራት አራት እያደረገ ነበር። ለዚህም ግልጽ የሆነው ምክንያት ሁለቱ አንድ ላይ ሲሆኑ አርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ እርስ በርሳቸው እየተበረታቱ ተልዕኮአቸውን ከግብ እንዲያደርሱ ነው። ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አብሮ የሚሄድ ሃሳብ መሆኑን አምኖ በክርስትና አገልግሎታችን ከእኛ ጋር በቅርብ ሆነው እንዲሠሩ ሌሎችን እንዲያመጣ እግዚአብሔርን መጠየቅ ተገቢ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በይበልጥ ትርጉም ያለው የሚሆነው ከሌላ ሰው ጋር ለመወያያትና ሃሳብ ለሃሳብ ለመለዋወጥ ስንችል ነው። ምስክርነታችንም በድፍረት የተሞላ የሚሆነው ሁለት ሆነን ሳለን በእንድ ላይ መቆም ስንችል ነው። ሕይወትም የበለጠ ዘለቄታ ያለው የሚሆነው በሌሎች ፊት ስንኖረው ነው። የአንድ በእውነት ላይ የተመሠረተች መልካም ቤተ ክርስቲያን አካል ወይም አባል የመሆን እድል ካጋጠመህ ለመንፈሳዊ እድገት እመቺ ነው። አማኙን በእምነቱ ለማጠናከር እግዚአብሔር በክርስቶስ አካል ውስጥ በጣም ጥሩ የሆኑ ስጦታዎችን አስቀምጦአል። አስተማሪዎች መንፈሳዊ እድገትን የሚረዱ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው። ይህን የመሰለ መንፈሳዊ ትምህርት መከታተልም ለመንፈሳዊ እድገት ሊረዳ ይችላል።

(25). ኤፌ 4:11-12 ደግመህ አንብብ። ኢየሱስ አገልጋዮችን ለቤተ ክርስቲያን ለምን እንደሰጠ ግለጽ።

በአጭር አነጋገር አማኙ የተጠራው ከሌሎች ጋር ሕብረት በማድረግ ለማደግ ነው። 'ኮይኖንያ' የሚለው የግሪክ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ጠቃሚ ትርጉም ያለው ቃል ነው። የቃሉም ትርጉም መካፈል፣ ሕብረት ማድረግ፣ መረዳዳት ማለት ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ክፍሎች 1ዮሐ 1:3፤ ፊልጵ 1:5፤ ፊሊ 6 እና በ1ቆሮ 10:16-17 ይገኛል። እነኚህ ክፍሎች ስለ ሕብረት ጠለቅ ያለ ትምህርት የሚያስገኙ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ሕብረት ማድረግ፣ በዓለም ፊት መመስከርና የክርስቶስን ባሕርይ መካፈል ለመንፈሳዊ እድገት አስገራሚ የሆነ መንገድ ነው።

እምነትን ከሌሎች ጋር መካፈል

ዓላማ 10 ለክርስቲያን ምስክርነት ጠቃሚ የሆኑ አራት አቅጣጫዎችን ለመጠቆም።

በክርስትና ሕይወት እንደመመስከር የበለጠ የሚያደናግር ምናልባት አይኖር ይሆናል። ለጓደኞቻችን ስለ ክርስቶስ የመመስከር አስፈላጊነት ብዙ ጊዜ ይሰማን ይሆናል። ይህንን ሳናደርግ ስንቀር የጥፋተኛነት ስሜት ይሰማናል። መንፈሳዊ እድገታችንን የምንገልጽበትና በይበልጥ እያደግን የምንሄድበት መንገድ ስለ እምነታችን በመመስከር ነው።

ምስክርነት የምንሰጥበት የመጀመሪያውና ዋናው መንገድ በራሱ በሕይወታችን ነው። ዘ2ቆሮ 3:3 ላይ ሲናገር፡- እናንተስ በእኛ አገልግሎት የመጣችሁ የክርስቶስ መልእክት መሆናችሁ የታወቀ ነው። ይህም መልእክት የተጻፈው በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፣ እንዲሁም በሰው ልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት የተጻፈ አይደለም በማለት ይነግረናል። እንዲህ ዓይነቱ መልእክት ማንም

ሊያነበውና ሊያውቀው ይችላል። በእንድ በኩል የአማኝ ሕይወት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሊነበብ የሚችል ነው ሊባል ይቻላል።

(26). 1ጢሞ 4፡12 እና 1ተሰ 1፡7ን እንብብና በሁለቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ክርስቲያኖች የተጻፈው ቃል፦

ሀ. ምስክርነት ለ. ፍርድ ሐ. ጸጋ መ. ምሳሌ

ሰዎችን ልጅ ከማፍራት የሚያግዳቸው ሁኔታና ክርስቲያኖችንም ሌሎች ክርስቲያኖችን ከማፍራት በሚያግዳቸው ሁኔታ መካከል ታላቅ ተመሳሳይነት አለ። እነዚህም ሁኔታዎች፦

1. እንድ ትንሽ ልጅ አስፈላጊው እድገት ላይ ባለመድረሱ ምክንያት ልጅ ማፍራት እንደማይችል ሁሉ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን አለማደግ ሲኖር የምስክርነታችንን ውጤት ያግዳል።

2. ፍሬ ማፍራት በተቃራኒ ጾታ አባላት መካከል እንድነትና መዋሐድ እንደሚጠይቅ (ይህም መዋሐድ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በጋብቻ መሆን አለበት) ክርስቲያንም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ፍሬ ለማፍራት የሚችለው ከክርስቶስ ጋር በመዋሐድና እርሱን የሕይወቱ ጌታና አዳኝ አድርጎ ሲኖር ብቻ ነው።

3. በሽተኛ ከሆነ ወይም እጅግ አስፈላጊ ከሆነው የሰውነት ክፍሉ አካባቢ ከተጎዳ ሰውን ፍሬ ከማፍራት እንደሚከለክለው ሁሉ፣ የኃጢአትና የግዴለሽነት ኑሮም የአማኙን ፍሬ ለማፍራት የመርዳት ችሎታውን ያቃውሳል።

(27). በጸሎት መንፈስ ሆነህ በቆላ 4፡5-6 ላይ የተጻፈውን አንብብ። በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በምስክርነታችን ውስጥ ልንከተላቸው የሚገቡ አራት አቅጣጫዎች አሉ። በተጠቀሱት መሠረት ዘርዝረህ ፃፋቸው።

ሀ. _____
ለ. _____
ሐ. _____
መ. _____

በማስታወሻ ደብተርህ ላይ "መንፈሳዊ" በሚለው ስር "መመስከር" ለሚለው ርእስ ለወደፊቱ እንዲጠቅምህ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጻፍ። 1ጴጥ 3፡15፣ ማቴ 5፡13 እና ሉቃ 12፡11-12። እምነታችንን ለሌሎች ስናካፍል የራሳችንን እምነት እያጠናከርን እንሄዳለን። ***ይህ ሌሎችን ወደ ጌታ የሚያመጣ እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን፣ የእኛንም መንፈሳዊ እድገት ደግሞ የሚጨምር ነው።***

የመከራ ፈተና

ለእግዚአብሔር ያለን ውጤታማነት፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ሕይወታችን እንዲያድግ፣ እግዚአብሔር ባዘጋጀልን መንገድ [illegible] አስፈላጊ ነው።

ከዚህ በታች ባሉት ነጥቦች ላይ ራስህን ሰመገምግም፣ ለጠንካራ ጎንህ 'ጠ' የሚለውን ፊደል በመጻፍ፣ ለመካከለኛ ጎንህ "መ" ለደካማ ጎንህ ደግሞ "ደ"፣ እንደዚሁም ደግሞ ለውጥ ለሚያስፈልግህ "ለ" የሚለውን ፊደል በክፍቱ ቦታ በመጻፍ ራስህን በራስህ ገምግም።

	ጠ	መ	ደ	ለ
1. ራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት				
2. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት				
3. ጸሎት				
4. እንደ ክርስቶስ አገልጋይ መኖር				
5. ለመንፈስ ቅዱስ ራስን መስጠት				
6. ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለህ ግንኙነት				
7. መመስከር				

"እውነት" ወይም "ሐሰት"። መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" በመጻፍ እመልክት።

_____8. ኃጢአታችንን ብንናዘዝም ባንናዘዝም እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር በማለት ከስህተት ያነጻናል።

_____9. እንደ ታላቁ የጸሎት ሰው ጆርጅ ሙለር አባባል የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ከመጀመር ይልቅ ቀኑን በጸሎት መጀመር ይሻላል።

___10. ቅድስና የሚያመለክተው አማኙ ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት ነው።

ምርጫ። ለሚቀጥለው ጥያቄ ትክክለኛ የሆነ እንድ መልስ ስላለ ፊደሉን በማክበብ እመልክት።

11. አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተፃፈበት ቋንቋ የግሪክ "ኮይኖኒያ" የሚለው ቃል ከየትኛው ጠቃሚ ሃሳብ ጋር የተያያዘ ነው።

ሀ. መንፈሳዊነት ከሥጋዊነት ጋር ተቃራኒ ከመሆን ጋር
ለ. ከሕብረት፣ ቃሉን ከማካፈልና ከመረዳዳት ጋር
ሐ. በመከራ ውስጥ ከማደግ ጋር
መ. ከእግዚአብሔር ቃል እቅድ ጋር

አሞር- መልስ። በተሰጠው መስመር ላይ ትክክለኛውን መልስ ጻፍ

12. ሰዎች ፍሬ እንዳያፈሩ ወይም ልጆች እንዳይወልዱ ከሚያግዷቸው ሁኔታዎች ጋር ሊነጻጸር የሚችል አማኞች ሌሎች አማኞችን ለማፍራት እንዳይችሉ ከሚያግዱአቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሁለቱን ጻፍ። _____

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

1. በሁሉም ነገር የመጀመሪያውን ስፍራ

15. ለ

2. ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ጋር፥ በልብ ውስጥ የተሰወረውን አሳብና ምኞት

16. ኃጢአታችንን መናዘዝ ይገባናል፥ እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአታችንን ይቅር በማለት ከአመጻ ሁሉ ያድነናል።

3. ሀ

17. ሀ. ምሳሌውን እዩ።
ለ. ሦስቱ ሰዎች የወርቅ ምስልን እናመልክም ማለታቸው።
ሐ. የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ለመመለስ መወሰኑ።
መ. ሴትዬዋ ወደ ንጉሡ ለመሄድ መወሰኗ።

4. ሐ

18. ሀ

5. የእግዚአብሔርን ሕግ በልባችን መጠበቅ

19. ለ

6. መብራት፣ ብርሃን

20. እውነትን መግለጥና ወደ እውነት ሁሉ መምራት

7. ያበራል፣ አስተዋዮች

21. ለ

8. ሀ. እምነት ለ. እርሱን ለሚፈልጉት ሁሉ

22. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ

9. የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎቹን መገልበጥና እንበበዘ ዋና ነጥቦቹን መሳፍ።

23. ሀ

10. ሀ. አማኞች
ለ. ስፍራው ተናወጠ። እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው የእግዚአብሔርን መልእክት በድፍረት መናገር ጀመሩ።

24. ሁለት ሁለት እየሆኑ

11. ዳንኤል በየዕለቱ፥ ጸለየ

25. የእግዚአብሔርን ሰዎች ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት

12. እግዚአብሔር እንደሚፈልገው መኖርና ዘወትር እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ

26. መ

13. "ከጌታ ጋር በሚገባ ስለ መመላለስ" የምንፅፈው አንቀጽ

27. ሀ. በምታደርገው ሁሉ አስተዋይ መሆን።
ለ. እድልን ሁሉ በሚገባ መጠቀም።
ሐ. ንግግርህ ሁሉ አስደሳችና በጸጋ የተሞላ ይሁን።
መ. ትክክለኛ መልስ እንዴት እንደምትሰጥ እወቅ።

14. እንደ ጽድቅ ዓላማዎች

7 መሠረታዊ እውነቶችና ከዚያም ባሻገር

ትምህርት

መንገድህን ስተህ ጠፍተህ ታውቃለህ? ምናልባት በሜክሲ ውስጥ ወይም በዋሻ ውስጥ ወይም እንግዳ በሆንክበት መንደር ወይም ከተማ ሳለህ የመንገድህ አቅጣጫ ጠፍቶብህ ይሆናል። በፊት የነበርክበትን ቦታ ካለፍክ በኋላ ዙሪያውን ትገር እንደነበር ስህተትህን ትገነዘባለህ። በመንፈሳዊ ልምምዳችንም ይህ ዓይነቱ ነገር እውነት ሊሆን ይችላል። እንዳየነው ከሆነ ብዙ ክርስቲያኖች ለማደግ እንቢ ይላሉ። ሌሎች መንገዳቸውን እያውቁም። ወደ ፊት ለመሄድ ፈፅሞም ገዘም ብለው ዙሪያውን የሚሽከረከሩ ያመስላሉ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለክርስቲያኖች የተሰጠ አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ መመሪያ አለ። *በተማርነው ላይ መቆምና ከዚያም ወደ ፊት መቀጠል አለብን*። ያንኑ ትምህርት በመድገም መቀጠል የለብንም።

የክርስትና ልምምዳችን መሠረቱ ዋስትና ያለው ሊሆን ይገባል። ከዚያም በኋላ ከመሠረታዊ እውነቶች ባሻገር ለመገንባት መቀጠል አለብን።

የነፍስ ትምህርቱ አከፋፈል

- ብስለት፡ መገንባትና መተው
- ስድስት የመሠረት ድንጋዮች
- ማጠቃለያ

የነፍስ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ነፍስ ትምህርት ስትጨርስ እነዚህን ነገሮች ማድረግ መቻል አለብህ።

- የአማኙን መንፈሳዊ እድገት ሂደት መግለጽ።
- ስድስቱን የክርስትና ልምምድ መሠረታዊ ክፍሎችና ሥራቸውን መግለጽ።

የነፍስ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለባተኛውን ክፍለ ትምህርት በጥንቃቄ አንብብ።
2. በትምህርቱ ማጠናከሪያ ላይ የተሰጡትን መልመጃዎች በጥንቃቄ ከሰራህ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ።

3. በነፍስ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የመከራ ፈተና ከመለያህ በኋላ መልሶችህን በጥንቃቄ አርም። በትክክል ያልመለስካቸው ጥያቄዎች ካሉም ከልሳቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር

ክፍል ሁለት፡ መሠረታዊነትና መሠረቱ

ባለፈው ጥናታችን ላይ በዕብ 5:11-14 ላይ የተጻፈውን ደጋግመን ተመልክተናል። እዚህ ላይ በእንደኛው ነፍስ በመን ለነበሩ የዕብራውያን ክርስቲያኖች ሲጽፍ አለመብሰላቸውን ይናገራል። መልእክቱን ሲጽፍ አስፈላጊ የሆኑ እውነቶችን ያስተምራቸዋል። ሆኖም ግን ገና ሕፃንነታቸውን ያልጨረሱ በመሆናቸው የሚያቀርብላቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች ሊቀበሉ አልቻሉም። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን መልእክት ማለትም የመጀመሪያዎቹን ትምህርቶች ደጋግሞ ማስተማር እንደሚያስፈልግ ይነግራቸዋል። ለማደግ እንዲችሉ የእግዚአብሔርን ቃል አልተቀበሉም፣ የሚጠሰሩት ወተት ብቻ ነው።

ዓላማን መመልከት

ዓላማ 1 መንፈሳዊ ብስለት የሚጠይቀው ምን ዓይነት እምነት እንደሆነ ለመግለጽ።

በዕብ 6:1 ላይ ወደ ፊት ስለመነሳስ መልዕክቱን በመቀጠል፦ "እንግዲህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያውን ትምህርት ትተን፣ ፍጹም ወደ ሆነው ትምህርት እንለፍ"፣ እያለ ሀሐፊው ልመናውን ያቀረባል። ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን የሚያቀርቡት "ወደ ፍጹምና ወይም ወደ ብስለት" በማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተፃፈበት ቋንቋ "ብስለት" የሚለው ቃል ሲተረጎም "ሙሉ ስው ወደ መሆን ደረጃ ላይ መድረስ" ማለት ነው።

(1). በዕብ 6:1 ላይ በተጻፈው መሠረት ነፍቱን ቦታ ሙላ። ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፣ መሠረትን ደግመን _____ ፣ እርሱም ከሞት ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት ነው።

የሕንጻ ሠራተኛ በየዕለቱ ጊዜ የሚያባክነው እየደጋገመ መሠረቱን በመጣል ላይ ብቻ ከሆነ በሕንጻው ላይ ምን ዓይነት መሻሻል ሊያደርግ ይችላል? ምንም ዓይነት መሻሻል ሊደረግ አይችልም። በተመሳሳይ መንገድም አንድ አስተማሪ መሠረቱን ብቻ እየደጋገመ የሚጥል ከሆነ የትም ሊደርስ አይችልም።

በአዲስ ኪዳን ዘመን ታላላቅ አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸውን በሦስት ከፍለው ያስተምሩ ነበር። 1ኛ/ ጀማሪዎች 2ኛ/ መሻሻል በመድረግ ላይ ያሉ 3ኛ/ የዘለጠ መሻሻል በማድረግ ላይ ያሉ። የአማኙ ዓላማ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ወይም እየበሰሉ ከሚሄዱት መካከል ለመሆን ነው። ወይም የመጀመሪያዎቹን ትምህርቶች መደጋገም ከማያስፈልጋቸው ጋር ለመሆን ነው።

የዚህን የመንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ዓላማ ከብዙ አቅጣጫዎች በመመልከት እጥንተናል። እንደ ኢየሱስ በመሆን በእርሱ ጌትነት ስር የእኛን ሚና መቀበል ነው። በማስተዋል ማደግ ማለት ነው። ሁልጊዜ ከመማር ይልቅ እንዳንድ ጊዜም አስተማሪ መሆን ነው። መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ፍጹም የሆነ ጠቅላላ እውቀት ማለት እንዳልሆነ እትዘንጋ። ኃጢአት የሌለበት ፍጽምና እይደለም። *የሚያድግና ሃላፊነት የሚሰማው እምነት የሚጠይቅ ነው።* ሰረጅም ጊዜ እርሱን ስናውቀው ያመነው ማን እንደሆነ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል። እርሱን ለረጅም ጊዜ እያወቅን ስንሄድ እርሱን በይበልጥ በሕይወታችን እናንጸባርቃለን። የድሮ ጥፋቶች ተወግደው የመልካም ምግባሮች ጸጋ መታየትና ማዳበር አለባቸው።

ወደ ግብ እንዴት መድረስ እንደሚገባን ማወቅ

***ዓላማ** 2 ከራሱ ጥረት በተጨማሪ፣ የአማኙ መንፈሳዊ እድገት ምን እንደሚያካትት ለመግለጽ።*

በዕብ 6:3 ላይ፦ "ይልቅስ ወደ ፊት እንሂድ፣ እግዚአብሔር ቢፈቅድልን ይህንን እናደርጋለን" በማለት ይናገራል። ይህ አነጋገር የመልእክቱን ጸሐፊ ራሱን የሚጨምር ነው። ለዕብራውያን ክርስቲያኖች የሰጠው ምክር ብቻ ሳይሆን፣ የራሱም ዓላማ ወደ ፊት ለመሄድ ነው። ዕብራ 6:1 ላይ አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተፃፈበት ቋንቋ መጠቀስ ያለበት አንድ አስፈላጊ ነጥብ አለ። "ፍጹም ወደ ሆነው ትምህርት እንለፍ" የሚለው ፈሮ ከሚለው ግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ትርጉሙም መሸከም ማለት ነው። እዚህ ላይ ቃሉ ታዛዥነትን የሚያመለክት ሲሆን፣ "ብስለት ወደ አለው ትምህርት እንወሰድ" ማለት ነው።

ከዚህ ቃል ጥናት ሁለት አስፈላጊ ትምህርቶች ይገኛሉ። በመጀመሪያ *ወደ ፊት ማለፍ* በግል ጥረት ብቻ ሊከናወን የማይችል ነው። መንፈሳዊ ብስለት የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ ብርቱ ኃይል ስር በመሆን ነው። በዚህ ምንባብ ላይ የተገለጠው ፍሬ ነገር ብርቱ ስለሆነው ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል በግላችን ራሳችንን አሳልፈን የማስረከብን ሃሳብ የሚያንጸባርቅ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል ለእድገታችን በመሥራት ላይ መሆኑ ግልጽ ነው። እኛ ማድረግ ያለብን ራሳችንን አሳልፈን ለእርሱ መስጠት ብቻ ነው።

በራሳችን የምናከናውነው ነገር ቢሆን ኖሮ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት በጣም አስቸጋሪ ነገር ይሆን ነበር። እኛ ወደዚህ ግብ መወሰድ እንዳለብን በዕብ 6:1 የተጻፈውና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያነግሩናል።

ደራሽ ውኃ በሚመጣበት ፊት ለፊት ጀልባ ለመቅዘፍ ሞክረህ ታውቃለህ? ያ በጣም አስቸጋሪ ነው። በእንድ በኩል አማኙ እንደ ደራሽ ውኃ ከሆነው ከዓለም ሁኔታ ጋር መዋጋት አለበት። በመንፈሳዊ ነገሮች ግን ብርቱው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግስጋሴ አማኙን ወደ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ለማምጣት ነው። እኛ ማድረግ ያለብን ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር በፈቃዳችን መተባበር ብቻ ነው።

(2). በዕብ 13:20-21 የሚያስፈልጉንን መልካም ነገሮች ሁሉ የሚሰጠን ማን ነው? የሚሰጠንስ ለምንድነው?

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወደ ፊት የምንገሰገስበትን ምክንያት በይበልጥ ሲገልጽ እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን በእኛ እንዲያደርግ የሚገልጽ ነው። ግቡ የእኛ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ሲሆን ይህም ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ዓላማ ነው። ከዕብ 6:1 ላይ "ፈሮ" የሚለው የግሪክ ግሥ መማር የሚገባን ሁለተኛው ነገር ቀጣይ ድርጊትን የሚያሳይ መሆኑን ነው። ብርቱ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በኩል ወደ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት የሚያሳልፈን ወይም የሚያሻግረን ቀጣይ የሆነ ድርጊት እንጂ በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል አይደለም። በክርስቶስ ማደግ ወይም መብሰል በአንድ ጊዜ ወደ እኛ የሚመጣ ነገር አለመሆኑን ማወቁ ጠቃሚ ነው። የዚህ የመንፈስ ቅዱስ ድርጊት ዓላማ እኛን ወደ ሙሉ ብስለት የሚያደርስ መንፈሳዊ እድገት ነው። በዚሁ መንገድ የእኛም ራሳችንን ለእርሱ አሳልፎ መስጠት፥ ዘለቄታ ያለው እንዲሆንና የማያቋርጥ ሊሆን ይገባል። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፦ "ወደ መንፈሳዊ ብስለት ራሳችንን ለማሳለፍ ወይም ለማሻገር መፍቀዳችንን እንቀጥል በማለት ልንተረጉመው እንችል ይሆናል።"

መተው፡ ለመድረስ አስፈላጊ ነው

***ዓላማ 3** አማኙ በመንፈሳዊ እድገት ወደ ፊት ለመሄድ ነገሮችን ከመተዉ በፊት አማኙ በሕይወቱ መያዝ የሚገባውን ነገሮች ለይቶ ለማወቅ።*

ጀልባን በዛፍ ላይ ወይም በእንድ ሌላ ነገር ላይ በገመድ የምናስረው በባሕሩ ላይ ተንሳፎ ወደ ታች እንዳይወሰድ ነው። ጀልባውን ለማንቀሳቀስ ስንፈልግ ደግሞ ያሰርንበትን ገመድ መፍታት አለብን። ገመዱን ሳይፈታ እንደታሰረ ጀልባውን ለመቅዘፍ የሚሞክር ሰው ሞኝ ሰው ከመሆኑም በላይ የትም ሊደርስ አይችልም። ወደ ሌላ ቦታ ለመድረስ መነሻን ቦታ ትቶ መሄድ አስፈላጊ ነው። ወደ ክርስቶስ ሙላት ወይም ወደ መንፈሳዊ

እድገት መግለጽ እንዳለበት እያንዳንዱ አማኝ ያውቃል። የሕይወቱ ግብም የክርስቶስን ሙሉ ክብር ማየት ቢሆንም፣ ብዙ ክርስቲያኖች ግን ከመጀመሪያው ትምህርት ሳይንቀሳቀሱ እዮንም እዚያው መሠረቱ ላይ ናቸው።

ዕብ 6:1 ላይ የመጀመሪያውን ሀረፍተ ነገር ልብ ብሰን ብንመለከት፦ "መሠረትን መልሰን እንመሥርት" የሚል ተጽፎ እናገኛለን። በዚሁ ጥቅስ ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፦ "ስለ ክርስቶስ የተሰጠንን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ፍጹም ወደሆነው ትምህርት እንለፍ" በማለት ተናግሮአል። ለእድገት አስፈላጊው ነገር የልጅነትን ነገር መተው ነው። ልጆች እያደጉ ሲሄዱ ይጫወቱባቸው የነበሩትን አሻንጉሊቶችና ሌሎችንም የልጅነት መንገዶችን ይተዋሉ። "መተው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዝቅተኛ ክፍል ትምህርታችንን ትተን ጠለቅ ወዳሰ ወደ አዲስ ትምህርት ማለፋችንን ወይም ወደ ሌላ ክፍል መዛወራችንን ነው።

አስቀድመን መሠረቱ ጽኑ መሆኑን ሳናረጋግጥ እየገነባን መሄዱ ሞኝነት ነው። ይህንን ነገር ማወቅ መሠረቱ የጸና መሆኑን ለማየት ጉጉት እንዲያድርባቸው ያደርጋል። ከዚያም መሠረቱን እየደጋገሙ ከመማር ይልቅ በመሠረቱ ላይ መገንባት መጀመር ይችላሉ። በዚህ ጥናት መሠረታዊ እውነቶች ብለን በምንጠራቸው ላይ በአጭሩ በማተኮር፣ እነዚህ ነገሮች አዲስ ባይሆኑም በሕይወታችን ላይ መተግበር ዓላማችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

(3). በ1ቆሮ 3:11 ላይ ለክርስቲያን ልምምድ የተጣለው ብቸኛው መሠረት ምንድን ነው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ለ. ቤተ ክርስቲያን ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ

(4). በዕብ 6:1 ላይ በተጻፈው መሠረት ለመንፈሳዊ እድገት መተው ያለብን የክርስቲያን መልእክት _____ ይባላል።

ስድስት የመሠረት ድንጋዮች

ዓላማ 4 ከመንፈሳዊ ልምምዳችን ጋር ያለውን ግንኙነት በማስረዳት የተዘጋጀ የክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርት ማስተማሪያ መጽሐፍ "ካቴኪዝም" ምን እንደሆነ ለመግለጽ።

አንዳንድ መሠረታዊ ትምህርቶች ከሌሎች መሠረታዊ ትምህርቶች ይልቅ የበለጠ መሠረታዊ መሆናቸውን በዕብ 6:1-3 ላይ የተጻፈው ይነግረናል። እነዚህም "የመጀመሪያ ትምህርቶች" ወይም ስለ ክርስቶስ የተነገሩ "የመጀመሪያ ቃላቶች" ሲሆኑ፣ ዓላማውም ወደ እውነተኛ መንፈሳዊ እድገት ለመጓዝ ነው። በክርስትና መሠረታዊ ትምህርት እውነተኛ

መሠረት መጣሉን እርግጠኛ ካልሆንን ግን ይህንን ለማድረግ ተስፋ ማድረግ አንችልም። መሠረታዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የክርስትና እምነትን ሥርዓት ለመያዝ አስፈላጊ ነው።

(5). በዕብ 6:1-2 ላይ የተጻፈውን በጥንቃቄ ካነበብክ በኋላ በዚህ መሠረታዊ ትምህርት ላይ የተጠቀሱትን ስድስቱን የመሠረት ድንጋዮች ዘርዝር። ከዚያም መልስህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጠው መልስ ጋር አስተያይ።

ሀ. _____
ለ. _____
ሐ. _____
መ. _____
ሠ. _____
ረ. _____

በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች እነዚህን የመሠረት ድንጋዮች የሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርትን ለማስተማሪያ እንደሚጠቀሙ ባቸው በጣም የጥንት የሆኑ መዛግብቶች ይነግሩናል። የሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርት ማስተማሪያ (ካቴኪዝም) የተዘጋጀው የመጀመሪያ የሆነውን የክርስትና ሥርዓተ ትምህርት ለአዲስ ክርስቲያን በማስተማር ለሥርዓተ ጥምቀት እንዲዘጋጅ ለማድረግ ነው። ሆኖም ግን እነኚህ የመሠረት ድንጋዮች ሁሉንም የመጀመሪያ የክርስትና ትምህርቶች ለአዲሱ አማኝ ያካትታሉ ብሎ ማንም ሃሳቡን አይሰጥም። እነዚህ ስድስት የመሠረት ድንጋዮች በመሠረቱ በሦስት ደረጃ ተመድበው እያንዳንዱ ሁለት ክፍል አለው። የመጀመሪያው የመሠረት ድንጋይ የሚጣለው ክርስቲያን በመሆን ነው። የሚቀጥሉት ሁለቱ የመሠረት ድንጋዮች ክርስቲያን በሕይወቱ ሊለማመዳቸው የሚገቡ ነገሮች ምሳሌ ናቸው። ስለ ወደፊቱ የሚናገረው አስተምህሮ ደግሞ ሦስተኛው ምድብ ይሆናል። ለጥናት አመቺ ይሆን ዘንድ በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት መሄዱ ይጠቅማል።

የወደፊቱን የሚያሳይ መግለጫ	—> የሙታን ትንሣኤ	—> ዘላለማዊ ፍርድ
የክርስትና ሕይወት ልምምዶች	—> ጥምቀቶች	—> እጅ መጫን
ክርስቲያን የሚከናወኑት ሁኔታዎች	—> ንስሐ መግባት	—> በእግዚአብሔር ማመን

ክርስቲያን ለመሆን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች

ከማይጠቅሙ ሥራዎች ንስሐ መግባት

ዓላማ 5 ለደኅንነት የሚያስፈልገው ንስሐ ምን ዓይነት እንደሆነ ለመግለጽ።

ክርስቲያን ለመሆን በመጀመሪያ የምንጥለው የመሠረት ድንጋይ ከንቱ ከሆኑ ሥራዎች መመለስ ነው። ይህንንም የምናደርገው ንስሐ በመግባት ነው (ዕብ 6:1)። በዚህ ጥቅስ ንስሐ መግባት ለሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ "ሜታኖይን" ይባላል። ይህ የግሪክ ቃል በታሪክ ዘመኑ ሁሉ አንድ ግልጽ የሆነ ትርጉም የያዘ ሲሆን ትርጉሙም "የአንድን ሰው ሃሳብ መለወጥ ወይም መቀየር" ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ስለ ንስሐ መግባት ሲናገር ጠበቅ አድርጎ የሚያተኩረው ውሳኔ ላይ እንጂ ስሜት ላይ አይደለም። ብዙ ሰዎች ስለ ንስሐ ያላቸው አስተሳሰብ ከስሜት ጋር በመሆኑ እንባን በማፍሰስ ለራሳቸው ያላቸውን ሃዘን መግለጽ ይሞክራሉ። ሌሎች ደግሞ ስለ ንስሐ የሚያስቡት ከሃይማኖት ሥርዓት ጋር አያይዘው ስለሆነ ሥርዓቱ የሚጠይቀውን "ዋጋ ለመክፈል" በመጨነቅና በመጠበብ ሥጋቸውን በመጉዳት ይታገላሉ። በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ አልፈውም፥ አልቅሰውም የገቡት እውነተኛ ንስሐ ላይሆን ይችላል። ንስሐ ማለት ጽኑ የሆነ የውስጥ ውሳኔ ወይም የሃሳብ ለውጥ ማለት ነው።

በብሉይ ኪዳን ንስሐ የሚለው ቃል የሚተረጎመው "ቀኝ ኋላ ዞሮ አቅጣጫን በመቀየር መመለስን" ነው። አዲስ ኪዳን የሚያተኩረው በውስጣዊ ውሳኔ ላይ ሲሆን፣ ብሉይ ኪዳን ደግሞ የሚያተኩረው ውጫዊ ድርጊት ላይ ነው። ሁለቱን በአንድ ላይ ስናደርጋቸው *ንስሐ* ማለት "አቅጣጫን ቀይሮ መመለስን የሚያስከትል፥ ውስጣዊ የሃሳብ ለውጥ" ማለት ነው። በዚህም ውስጥ ወደ አዲስ አቅጣጫ መንቀሳቀስ እንጀ ምራለን። ይህ ዓይነቱ ንስሐ ለኃጢአተኛ ሰዎች ደኅንነት አስፈላጊ ነው።

(6). በሉቃ 15:11-32 ላይ የተጻፈውን ታሪክ ካነበብክ በኋላ በቁጥር 18 ላይ የጠፋው ልጅ ያደረገውን *ውስጣዊ ውሳኔ* በራስህ ቃላት ጻፍ።

(7) ሉቃስ 15:20ን አንብብና፥ የጠፋው ልጅ የልቡን ውስጣዊ ውሳኔ እንዴት በሥራ እንደተረጎመ ግለጽ።

ኃጢአተኛ ሰው በሕይወቱ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ጀርባውን እንዳዞረ ቀደም ሲል ተመልክተናል። የሚወስደው እርምጃ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚያርቀው እንጂ የሚያቀርበው አልሆነም። ስለዚህ ኃጢአተኛ ሰው በሁለት መንገድ መለወጥ አለበት። ሃሳቡን መለወጥ አለበት፣ አቅጣጫውንም መለወጥ አለበት። ከኃጢአቱም ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት።

ማቴ 27:3-4 አንብብ፥ ይሁዳ ላደረገው ነገር እንደተጸጸተ ይናገራል። ይህ "ተጸጸተ" የሚለው ቃል በግሪክ ያየነው ቃል አይደለም። እዚህ ላይ የተገለጠው ንስሐ ስለመግባቱ ሳይሆን "ባላደረግሁት ኖሮ፣ በቀረብኝ ኖሮ" የሚለውን የሀዘንን ስሜት የሚያመለክት ነው። ውስጣዊ ዝንባሌውን ወይም ውጫዊ አቅጣጫውን አለመቀየሩን የሚገልጽልን በሚቀጥለው ቁጥር ላይ "ሄዶም ታንቆ ሞተ" የሚለው ነው።

(8). *መጥምቁ* ዮሐንስ የተሳከው ለኢየሱስ ክርስቶስ *መምጣት* መንገድ *ስማዘጋጀት* ነው። የሰበከውም ልዩ ጥምቀት ነበር። በማር 1:4 ላይ ሕዝቡ ስለ ኃጢአታቸው ምን እንዲያደርጉ ነበር የነገራቸው?

ሀ. ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ
ለ. የእግዚአብሔርን *መንገዶች* እንዲማሩ
ሐ. ስላደረጉት ጥፋት እንዲያዝኑና እንዲያሰቅሱ

(9). ማር 1:15ን አንብብ። ስለ ኃጢአታችን ምን ማድረግ እንደሚገባን ነው ኢየሱስ የሰበከው?

በአዲስ ኪዳን በማንኛውም ስፍራ ንስሐ መግባት ሰው ለወንጌል ቃል የሚሰጠው የመጀመሪያ አስፈላጊ ምላሽ ነው። እግዚአብሔር ይህን ዓይነት ምላሽ ይጠይቃል። ስለዚህ የሚያስተምሩትን ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ለመጻፍ ከፈለግህ፦ የሐዋ 2:37-38፣ የሐዋ 20:20-21፣ና ሉቃ 13:3 ናቸው።

በክርስትና ሕይወታችን የጣልነውን የመጀመሪያ የመሠረት ድንጋይ ለማስተዋል ምን ዓይነት ንስሐ እንደገባንና እንደተመለስን የሚያስረዳውን ልብ ብሎ ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ንስሐ የገባነውም ከሞት ሥራ ወይም ከንቱ ከሆኑ ሥራዎች ነው። መላው ዓለም "ሃይማኖተኛ" ነው። ሰው ሁሉ የሚያመልከው ነገር አለው። ስለዚህ በአለም ላይ ብዙ ዓይነት "የሃይማኖት ሥርዓቶች" አሉ። ሰዎች የተለያዩ አማልክቶችን በማምለካቸው በሃይማኖታዊ ተግባራቸው ቸርነትና ምሕረት እንዲደረግላቸው በጉጉት ይጠብቃሉ። እነዚህ ሁሉ የማይጠቅሙ የሞት ሥራዎች ናቸው።

(10). ሞትን የሚያስከትሉ ሥራዎች ደግሞ አሉ፣ በኤፌ 2:1 ላይ በተጻፈው መሰረት ሰዎችን በመንፈሳዊ ነገር የሞቱ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

በቆላ 2:13 ላይ፦ "በአንድ ወቅት በኃጢአታችሁ የተነሣ ሙታን ነበራችሁ" ይላል። የሰው ድርጊቶች ከእግዚአብሔር የሚለዩት ሆነዋል። የሰው ድርጊቶች ወግና ሥርዓት ቢኖራቸውም፣ ቅዱስ የሆነውን የአምላክን ፍላጎት ይቅርና የሰውን መሠረታዊ ፍላጎት እንኳ ለማሟላት ኃይል የላቸውም።

በእግዚአብሔር ማመን

ዓላማ 6 በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ ምን እንደሚቀበል ለመግለጽ።

በክርስትና ሕይወታችን የምንጥለው ሁለተኛው የመሠረት ድንጋይ በእግዚአብሔር የማመንን መሠረት ነው (ዕብ 6:1)። ኢየሱስ በዮሐ 6:47 ላይ፦ "በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው" በማለት ተናገረ። *ማመን* ማለት በአንድ ሰው ላይ ወይም በአንድ ነገር ላይ እምነታችንን መጣል ማለት ነው። በዕብ 11:1-2 ላይ "እምነት ማለት በተስፋ የምንጠባበቃቸውን ነገሮች እንደምናገኝ የሚያረጋግጥ፣ የማናያቸው ነገሮች ስለመኖራቸው የሚያስረዳ ነው። የቀድሞ ሰዎች የተመሰገኑት በእምነት ምክንያት ነው።"

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *በክርስቶስ ስለማመን* ከተሰጡት ጥሩ መግለጫዎች መካከል አንዱ በዮሐንስ 3:14-21 ላይ የተጻፈው ታሪክ ነው። ይህንን ክፍል አንተም እንደምትወደው አምናለሁ።

(11). በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ ምን ይቀበላል?

(12). በዮሐ 3:18 እንደተጻፈው ሰው ለምን ይፈረድበታል?

ሀ. በኃጢአቱ ምክንያት
ለ. የቤተ ክርስቲያን አባል ባለመሆኑ
ሐ. በእግዚአብሔር ልጅ ባለማመኑ
መ. የጽድቅን ሥራ ባለመሥራቱ

"በእግዚአብሔር ማመን" የሚለው ሐረግ መጽሐፍ ቅዱስ በተፃፈበት በመጀመሪያ ቋንቋ "ወደ እግዚአብሔር የመመራትን ሃሳብ" የሚያንጸባርቅ ነው። ስለሆነም እምነታችን ወደ እግዚአብሔር በመሆኑ በዚያ ውሳኔ ላይ ማረፋችንን የሚያስረዳ ነው።

አንድ ታላቅ አገልጋይ የሆነ ሚሲዮናዊ ለሚያገለግላቸው ሰዎች የዮሐንስን ወንጌል በቋንቋቸው ለመተርጎም ሲሞክር "ማመን" ለሚለው ቃል ተስማሚ የሆነ ቃል አጣ። በዮሐንስ ወንጌል ላይ ይህ ቃል በብዛት ተጽፎ ይገኛል። "ማመን" ለሚለው በነዚህ ሰዎች ቋንቋ ቃል ሊያገኝለት ባለመቻሉ በጣም ተቸገረ። አንድ ቀን የአገሬው ተወላጅ የሆነ ሰው ወደዚህ ሚሲዮናዊ ቤት መጣ። ሰውየው በጸሐይ ሲሰራ ውሎ በጣም ደክሞት ነበርና ወንበር ላይ ዘፍ አለና በቋንቋው፦ "ራሴን መሸከም ስላቃተኝ፥ ክብደቴን ሁሉ በወንበሩ ላይ አደረግኩኝ፥ ወንበሩ ችሎ ተሸከመኝ ሲል ተናገረ።" በዚህን ጊዜ ሚሲዮናዊው ከተቀመጠበት ብድግ አለና፦ የምፈልገው ቃል ይህ ነው በማለት ተናገረ። እምነት ማለት መላው

ክብደታችንን፣ መላው አካላታችንን፣ ተስፋችንን፥ አዳኛችን በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መጣል ማለት ነው።

የክርስትና ሕይወት ልምምዶች

ሌላው ሁለተኛው የመሠረት ድንጋይ ደግሞ አማኞች ጌታን በተቀበሉበት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የደነገገውን ሥርዓት መፈጸም ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትጠብቃቸው የተለያዩ ሥርዓቶች አሉ። ከሥርዓቶቹም መካከል ጥምቀትና የጌታችን ራት የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ስለ ጥምቀት ማስተማር

ዓላማ 7 በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቃችን ዓላማ ምን እንደሆነ ለመግለጽ።

በዕብ 6:2 መሠረት ስለ ጥምቀት የሚሰጠው ትምህርት መሠረት ከሆኑት የክርስትና ትምህርቶች ውስጥ አሳባቢና አንዱ ክፍል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ የጥምቀት ዓይነቶች ተጠቅሰዋል። ከተጠቀሱትም ውስጥ የመጥምቁ ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት፣ የክርስቶስ ጥምቀትና የመከራ ጥምቀት የመሳሰሉት ይገኙበታል። ክርስቲያን ማተኮር ያለበት ሦስት መሠረታዊ ጥምቀቶች ላይ ሲሆን፣ እነርሱም (1) በአዲስ ልደት ወደ ክርስቶስ አካል መጠመቅ፣ (2) ክርስቶስን ለመቀበላችን ውጪያዊ ማስረጃ አድርገን የምንመሰክርበትን የውኃ ጥምቀት (3) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት።

(13). በአዲስ ልደት በክርስቶስ አካል ውስጥ መጠመቅ ማለት ምን እንደሆነ በ1ቆሮ 12:11-13 ላይ የተጻፈው ትምህርት ይሰጠናል። በዚህ ጥቅስ መሠረት እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን_____። ሁላችንም አንዱን _____ጠጥተናል።

በ1ቆሮ 12:11-13 ላይ *አንድ፣ አንዱን* የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስህ አስምርበት። አማኞች ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ስላላቸው ሕብረት የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሁላችንም ልናስታውሰው የሚገባን በገላ 3:26-28 ላይ ያለውን ነው። "ሁላችንም ከክርስቶስ ጋር ሕብረት አግኝተን የእግዚአብሔር ልጆች የሆነው በእምነት ነው። ወደ ክርስቶስ ሕብረት ሁላችንም ተጠምቀናል። ስለዚህ በአይሁድና በአሕዛብ፣ በባሪያዎችና በነፃ ሰዎች፣ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት የለም። ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ሕብረት ሁሉም አንድ ናቸው።"

ልናውቀው የሚገባን ሁለተኛው ጥምቀት ደግሞ የውኃ ጥምቀት በመሆኑ ለመረዳት አስቸጋሪ አይሆንም። ጥምቀት ትርጉም ያለው መሆን እንዳለበት ክርስቲያኖች ሁሉ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው። ጥምቀት ባዶ የሆነ ትርጉም የሌለው ሥርዓት መሆን የለበትም። አንድ ሰው ክርስቶስን በመቀበል እንደገና ከመንፈስ ሲወለድ ውስጣዊ የሆነ ሥራ በመሆኑ የማይታይ ነው።

ይህንን ውስጣዊ የሆነ ሥራ የሚለማመደው ሰው በውኃ በመጠመቅ በውጫዊ መንገድ እንዲያሳይ ታዟል።

(14). ሐዋ 2:38ን አንብብ። ከዚሁ ካነበብከው ውስጥ በውኃ መጠመቅ ለአማኝ ለምን እንደሚያስፈልግ ገልጽ።

(15). በ1ጴጥ 3:21 ላይ እንደተጻፈው "የውኃ ጥምቀት የአካልን እድፍ የምናስወግድበት ሳይሆን፣" ጥምቀት ምን እንደሆነ ነው የሚናገረው?

የውኃ ጥምቀት ምን እንደሆነ በደንብ የሚያብራራው በሮሜ 6:1-4 ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደሚነግረን አንድ አማኝ በውኃ በሚጠመቅበት ጊዜ ከክርስቶስ ጋር እንደሞተ፣ እንደተቀበረና እንደተነሣ ሰይጣ የሚያሳውቅበት ማስረጃ ነው። በጥምቀት ጊዜ አማኞች የምንጠልቅበት ውኃ ልክ እንደመቃብር ነው። በዚያ በውኃ ውስጥ በምንጠመቅበት ጊዜ በእምነት አሮጌው ሕይወታችንን በመቅበር ከጠለቅንበት ውኃ ውስጥ ስንወጣ ደግሞ በአዲስ ሕይወት ከክርስቶስ ጋር መነሣታችንን እንመሰክራለን። ክርስቶስ በእባቱ ክብርና ኃይል ከሞት እንደተነሣ እኛም በአዲስ ሕይወት ለመኖር ከእርሱ ጋር መነሣታችንን እንገልጻለን።

ልናጠናው የሚገባን ሦስተኛው ጥምቀት ደግሞ ኢየሱስ በሐዋ 1:5 ላይ። "ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ነገራቸው ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ዮሐንስም ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት። "እነሆ እኔ ሰንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፣ ነገር ግን ከእኔ በኋላ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል" በማለት እስቀድሞ በማቴ 3:11 ላይ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በዘጎለ ሃምሳ ዕለት እንደተከናወነ በሐዋ 2 ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይነግረናል።

ይህ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀረበው በተለያየ አንጋገር በመሆኑ ግራ መጋባት የሰብንም። በኢዩ 2:28-29 ላይ እንደ መፍሰስ ሲገለጥ፣ በኤፌ 5:18 ላይ እንደ መሞላት ተገልጠአል። በሆሴ 6:3 ላይና በያዕ 5:7 ላይ ደግሞ የተነገረው እንደኋለኛ ዝናብ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ የተሰፋ ቃል ለመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ብቻ ሳይሆን፥ ለሌሎችም እንደሆነ ለይተው በግልጽ የሚያሳዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። እነዚህም በሐዋ 8:14-17 ላይ የተጠቀሱት የሰማርያ ሰዎች፣ በሐዋ 9:17 እና በ1ቆሮ 14:18 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ በሐዋ 10:44-48 ላይ የቆርኔሌዎስ ቤተሰብ፣ በሐዋ 19:1-7 ላይ የተጠቀሱት የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት ናቸው። *የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዓላማ ክርስቶስን በሕይወታችን ከፍ ለማደረግ፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት፣ መንፈሳዊ ፍሬዎችን በሕይወታችን ለማፍራትና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ኃይል ለመቀበል ነው።*

ስለ እጅ መጫን ማስተማር

ዓላማ 8 ከእጅ መጫን ልምምድ ጋር የሚመጡትን ልዩ በረከቶችና ኃላፊነቶች ለመግለጽ።

የእግዚአብሔር ቃል መሠረታዊ እውነት አድርጎ የሚቆጥረው ሌላው ክርስቲያናዊ ልምምድ ስለ "እጅ መጫን" የሚሰጠው ትምህርት ነው (ዕብ 6:2)። በብሉይ ኪዳን ዘመን በእይሁድ ልምምድ ይህ የእጅ መጫን ሥርዓት ኃጢአትን፣ የሰውን በደል፥ መሥዋዕት ወደሚሆነው እንሰሳ ላይ የማስተላለፊያ መንገድ ምልክት ነበር። ከዚህም በላይ እጅ መጫን አንድን ሰው ለተለየ ለእግዚአብሔር እገልግሉት ለመለየትና ለዚያ ሰው ልዩ በረከትን የማስተላለፊያ መንገድ አድርገው ይጠቀሙበት ነበር። የመጨረሻ ሁለቱ የእጅ መጫን ሥርዓት ልምምድ በአዲስ ኪዳን ዘመንም ሊገለገሉበት ቆይተዋል።

ኢየሱስ እጁን በሕፃናት ላይ በመጫን ባረካቸው (ማር 10:16)። ሌሎችም ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመባረክ ሲሉ እጃቸውን በሰዎች ላይ ጭነዋል። በሐዋ 19:6 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እጁን በሚነካቸው ጊዜ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል።

(16). በያዕ 5:14-15 ላይ በተጻፈው መሠረት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች "ዘይት ቀብተው" በሚጸልዩበት ጊዜ ለታመመ ሰው የሚሰጡት በረከቶች ምንድን ናቸው?

እንድን ሰው ለተለየ አገልግሎት ለመለየት ሲፈለግ እጅ በመጫን ነበር የሚጠቀሙት። ይህም ለአገልግሎት ሹመት እንደመቀበል የሚቆጠር ሲሆን በኃላፊነት ስፍራ ላይ አንድን ሰው ማስቀመጥ ነው።

(17). በሐዋ 6:1-6 ላይ እንደተጻፈው እጅ በመጫን ለተለየ ሥራ የተመረጡት እነማን ነበሩ?

ሀ. ሐዋርያት
ለ. የተለየ ሥራ ለመሥራት የተመረጡ ሰባት ሰዎች
ሐ. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች

(18). በሐዋ 13:1-3 ላይ እንደተጻፈው ሁለት ሰዎች ለልዩ ሥራ እንዲለዩ የጠየቀው ማነው?

(19). በዚህ ምንባብ ውስጥ እጅ በመጫን ለተለየ ሥራ የተመረጡት እነማን ነበሩ?

የእነዚህ የሦስት ዓይነት ጥምቀቶችና የእጅ መጫን ልምምድ መሠረታዊ እውቀት እንዲኖረን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ ነገሮች የሚናገረውን መከታተል በጣም ጠቃሚ ነው።

የወደፊቱ መግለጫዎች

በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ ከስድስቱ የመሠረት ድንጋዮች አሁን የምንመለከተው የመጨረሻ ሁለቱን እውነቶች ነው። እነርሱም "የሙታን ትንሣኤና ዘላለማዊ ፍርድ" እንደሆኑ በዕብ 6:2 ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይነግረናል። እነዚህ እውነቶች በአንድ ላይ ሲወሰዱ የአሁኑ ድርጊቶቻችን ዘለቄታ ያለው ውጤት እንደሚኖራቸው የሚያስረዱ ናቸው። ምድራዊ ሕይወታችንን ከዘላለማዊው አንጻር ማስተያየት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚናገሩ ናቸው። እነዚህ የሰውን የአሁኑን ሃላፊነት የሚናገሩ የመሠረት ድንጋዮች ናቸው።

የሙታን ትንሣኤ

ዓላማ 9 አማኞች ከሙታን እንደሚነሡ የተሰጠውን ማረጋገጫ ለማመልከት።

ስለ ሙታን ትንሣኤ የሚሰጠው ማንኛውም ትምህርት በዓለም ላይ ዘወትር ክርክር እንዳስነሣ ነው። ኢየሱስ በዚህ ዓለም በነበረበት ዘመን እንኳ በትንሣኤ የማያምኑ አንድ የተለዩ የአይሁድ ቡድን ነበሩ። የሙታን ትንሣኤ በሰው ላይ ሃላፊነትን የሚያኖር ትምህርት ነው። አንዳንድ ሰዎች ትንሣኤ እንደሚኖር አለማወቁን ቢመርጡም፣ ጥልቅ የሆነው የሰው መንፈስ ግን ከሞት በኋላ የሕይወት ተስፋ መኖሩን ያውቃል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለእኛ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው። በ1ቆሮ 15:12-26 ላይ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የእኛ ትንሣኤ ከኢየሱስ ትንሣኤ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳለው የሚያሳይ ነው።

(20). በ1ቆሮ 15:15 መሠረት ጳውሎስ የክርስቶስን ትንሣኤ ከእኛ ትንሣኤ ጋር እንዴት እንድሚያገናኘው በራስህ ቃላት ጻፍ።

ጳውሎስ ስለ ትንሣኤ በ1ቆሮ 15:20 ላይ የሚናገረውን ጠበቅ አድርጎ ለመግለጽ፦ "አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።" በሐዋ 4:2 ላይም የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የተሰበከው ሙታን እንደሚነሡ ለማረጋገጥ ነበር።

(21) በ1ጴጥ 1:3-5 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት አማኙ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በኩል የተሰጠው ምንድን ነው?

የሐዋርያው ጳውሎስ ትልቁ ምኞት፦ "ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኃይል ለማወቅ ነበር" (ፊልጵ 3:10)። እኛም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን በትንሣኤው ኃይል ልናውቀው ይገባናል። ሮሜ 6:4 ላይ እንደሚያስረዳን የውኃ ጥምቀታችን እንኳ ከክርስቶስ ትንሣኤና ከአዲስ ሕይወታችን ጋር የተያያዘ ነው።

የዘለዓለም ፍርድ

ዓላማ 10 በክርስቶስ መሥዋዕትነት ማመናችን ከዘላለማዊ የሞት ቅጣት ለምን ነፃ እንደሚያወጣን ለመግለጽ።

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው *የሙታን ትንሣኤና የዘላለም ፍርድ* ከስድስቱ የመሠረት ድንጋዮች ውስጥ የመጨረሻዎቹ መሠረታዊ እውነቶች ናቸው። በሐዋ 17:31 ላይ ስለ ሁለቱ በግልጽ ሲናገር፦ "እርሱ በመረጠው ሰው አማካኝነት በዓለም ሁሉ ላይ በእውነት የሚፈርድበትን ቀን ወስኖአል፤ ይህንንም ያረጋገጠው ያንን የመረጠውን ሰው ከሞት በማስነሣቱ ነው" ይላል። የእግዚአብሔር የፍርድ ሂደት በሰው ፊት በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚከናወነውም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱ ቢያንስ ሰባት ፍርዶች ሲኖሩ፣ እነርሱም፦

1. ኃጢአተኛ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ሊቀበል የሚገባውን ፍርድ፣ ክርስቶስ ምትክ በመሆን በመስቀል ላይ የተቀበለው ፍርድ ነው። የኃጢአተኛ ምትክ በመሆን የሞት ፍርዱን ተቀበለ። እንግዲህ በእርሱ መሥዋዕት የሚያምኑት ሁሉ ከዘላለማዊ የሞት ቅጣት ነፃ ይሆናሉ (ዮሐ 5:24)።

2. ሌላው አማኝ አውቆ በፈቃዱ ለጌታ ባለመታዘዝ የሚቀበለው ፍርድ ወይም ቅጣት ሲሆን፣ በዕብ 12 ላይ ስለዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ በተለይ የሚሰጠውን ምክርና ትምህርት መከተል ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም በ1ቆሮ 11:31-32 ላይ የተጻፈውን ተመልከት።

3. የእስራኤል ፍርድ (ሕዝ 36:16-21)።

4. በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት አማኞች የሚቀበሉት ፍርድ (2ቆሮ 5:10)

5. በዓለም መጨረሻ የሚሆነው ፍርድ (ማቴ 25:31-46)።

6. የወደቁ መላእክት ፍርድ (ይሁዳ 6)።

7. ያላመነው ዓለም ፍርድ የሚቀበልበት ስፍራ የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ (ራዕ 20:11-15)።

ማጠቃለያ

እንኚህ ባጭሩ ያጠናናቸው እውነቶች ለክርስትና ልምምዳችን መሠረት መሆናቸውን እናስታውስ! ልጆች ሕንፃ ሲገነቡ በእሽዋ ላይና በቀላሉ ሊፈርስ በሚችል ነገር እንደሚገነቡ እኛም ወደ መንፈሳዊ ብስለት እየተንቀሳቀስን፥ መሠረቱን በማነፅ ካንዱ ወዳንዱ ማለፍ አለብን እንጂ እየደጋገምን መሠረቱን እንዳንዞር መጠንቀቅ አለብን። ሆኖም እያንዳንዱ አማኝ መሠረቱን አጥብቆ መመስረት ያስፈልገዋል። አጠንክረን ሳንመሠርት በላዩ መገንባት የለብንም። መሠረቱ ጠንካራ ከሆነ ወደሌላው ማለፍ አለብን። የዕብራውያን ፀሐፊ ለዕብራውያን አማኞች ሲፅፍላቸው ሁለቱም ማለትም የክርስትና አስተምህሮ የክርስትና ልምምዶች ለመንፈሳዊ እድገት አስፈላጊ መሆናቸውን እንዳሳያቸው እናያለን።

በመስቀል ላይ የነበረው ወንበዴ፣ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ሴት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ የፊሊጵስዩስ የወህኒ አዛዥ - ሁሉም የተለየና የተራራቀ ልምምዶች ነበሩአቸው። እኛም የራሳችን የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሆነ ልምምዶች እንዳሉን እናውቃለን። በተጨማሪ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርትም አስፈላጊ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች፣ በአዲስ ኪዳን እንደ አጽሉስ ያሉ ከልባቸው የሚያስተምሩ ነበሩ። ነገር ግን ብዙ እውቀት አልነበራቸውም። ስለዚህ ወደ እውነተኛው የክርስቲያን ባሕርይ ወደፊት ማደግና መገንባት አለብን። ከዚያም እውነት የሆነው፥ ሕይወት ማለትም የክርስቶስ ነፀብራቅ በእኛ ሕይወት ውስጥ ይታያል። ይህ ዓይነቱ ሀንፃ ነው በመሠረቱ ላይ መገንባት ያለበት። ይህም በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚታይ እግዚአብሔርንም የሚያከብር ነው።

የመከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት። መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" የሚለውን ፊደል በክፍቱ ስፍራ ጻፍ።

_____1. አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ ካለበት ያለ እግዚአብሔር እርዳታ በራሱ ጥረት ብቻ ሊያድግ ይችላል።
____2. አማኙ መሠረታዊ እውነቶችን ከመሠረተ በኋላ በነዚህ መሠረታዊ እውነቶች ላይ እየገነባ ወደፊት መቀጠል አለበት።
____3. የክርስትና መሠረታዊ ትምህርት (ካቴኪዝም) የተዘጋጀው ለሥርዓተ ጥምቀት የተዘጋጁ ይሆኑ ዘንድ አዲስ አማኞችን ለማስተማር ነው።
____4. ንስሐ በይበልጥ ከስሜት ጋር የተያያዘ ነገር ነው።
____5. የክርስትና አስተምህሮ የውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥን በማስገኘት ውጫዊ ቀኝኋላ መዞርን ወይም መመለስን የሚያስከትል ነው።
____8. የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ድንጋጌ ቤተክርስቲያን እንድትጠብቀው እግዚአብሔር ያዘዛት ሥርዓት ነው።
___7. ኢየሱስን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ከተቀበሉ በኋላ ለአማኞች ምንም ዓይነት ፍርድ የለባቸውም።

8-13 አማኙ የሚጥለውን ስድስቱን የመሠረት ድንጋዮች በትምህርቱ ላይ እንደተጠቀሰው በቅደም ተከተል አስፍራቸው።

ክርስቲያን የሚኮንበት ሁለት ሁኔታዎች፡-

8. _____
9. _____

የክርስቲያን ሕይወት ልምምዶች

10. _____
11. _____

የወደፊቱን የሚያሳዩ ሁለት መግለጫዎች

12. _____
13. _____

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. እንመሥርት

12. ሐ

2. የሰላም አምላክ፣ የእርሱን ፈቃድ እንድናደርግ

13. ተጠምቀናል፣ መንፈስ
3. ሐ

14. እግዚአብሔር ስላዘዘ አስፈላጊ ነው።

4. የመጀመሪያ ትምህርቶች

15. ከመልካም ሕሊና ለእግዚአብሔር የተገባ ተስፋ ነው።

5. ሀ. ከንቱ ከሆነ ሥራ መመለስ
   ለ. በእግዚአብሔር ማመን
   ሐ. ስለ ጥምቀት ማስተማር
   መ. እጅን ስለ መጫን ማስተማር
   ሠ. የሙታን ትንሣኤ
   ረ. ዘላለማዊ ፍርድ

16. የአካል ፈውስና የኃጢአት ይቅርታ

6. ወደ አባቱ ተመልሶ የመሄድ ውሳኔ
17. ለ

7. ተነሥቶ ወደ አባቱ በመመለስ

16. መንፈስ ቅዱስ
8. ሀ
19. በርናባስና ሳውል

9. ከኃጢአታችን መመለስ

20. ከሙታን የማንነሣ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣም እንደማለት መሆኑን ጳውሎስ ያመለክታል።

10. አለመታዘዛቸውና ኃጢአታቸው
21. በተስፋ የተሞላ አዲስ ሕይወት
11. የዘላለም ሕይወት

8 የክርስቲያን ባሕርይ ማስረጃ

ትምህርት

ወደ ትምህርታችን ማጠቃለያ እየተቃረብን በመሆኑ ዘመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን የምንሄድ መሆናችንን ማስረጃ ስለሚሆኑት ነገሮች እንመለከታለን። ቀደም ሲል እንደገለጽነው አንድ ልጅ በቤቱ ግድግዳ ላይ ምልክት እያደረገ ከአባቱ ቁመት ጋር በማነጻጸር የእድገቱን ሂደት ለመከታተል እንደሚሞክር እኛም የመንፈሳዊ እድገታችንን ሂደት ለመከታተል የመለኪያ ዘዴ መኖሩ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

"ማስረጃ" የሚለው ቃል ማረጋገጫ የሚሰጥ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያናዊ ማስረጃዎች ላይ የሚያተኩሩ ግልጽ የሆኑ ትምህርቶችን ያያዘ ነው። ብዙ ጊዜ ማስረጃ የሚቀርበው በሕግ ዙርያ ለፍርድ ቤት እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። ፍርድ ቤት የቀረበ ሰው ጥፋተኛ መሆን አለመሆኑን የሚረጋገጠው በማስረጃ ነው። የፍርድ ቤቱ ዳኞችም ማስረጃውን መርምረው መመዘን አለባቸው። ማስረጃው ሰውነኔ በቂ መሆን አለመሆኑን የመመዘኑ ኃላፊነት የዳኞቹ ነው።

አንድ ጊዜ አንዱ ሰው ሲጠይቅ- ክርስቲያን በመሆንህ ተከሰህ በዳኛ ፊት ብትቀርብ በአንተ ላይ ለማስፈረድ በቂ ማስረጃ ይገኝ ይሆን? ሲል ተናገረ። ይህ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በአንድ በኩል ሰፊው ዓለም ለዳኝነት ወይም ለፍርድ እንደተቀመጠ ሰው በመሆኑ የማያምኑ ሰዎች እንኳ ክርስቲያኑ እንደ እምነቱ ወይም በአፉ እንደሚናገረው በሕይወቱ ይኖር ወይም አይኖር እንደሆነ ለይተው ያውቃሉ። ይህም ክፍለ ትምህርት የሚያተኩረው የበሰለ መንፈሳዊ ሕይወት አጥጋቢ ማስረጃ ስለሆነው፣ በእማኙ ሕይወት ውስጥ ስለሚታየው ወይም ስለሚገለጠው የክርስቶስ ባሕርይ ነው

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ኢየሱስን ወደ መምሰል ማደግ
- እንደ ኢየሱስ መምሰል

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ፡

- የኢየሱስ ሕይወትና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማኙን ወደ ፍጹም መንፈሳዊ እድገት ለማምጣት እንዴት እንደሚረዱ መግለጽ።

- ድል አድራጊ ክርስቲያን መንፈሳዊ እድገቱን የሚያግዱ ነገሮችን እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል መግለጽ።

የነፍስ ትምህርት መመሪያዎች

1. 8ኛውን ነፍስ ትምህርት በጥንቃቄ አንብብ።
2. በትምህርቱ ማጠናከሪያ ላይ የተሰጡትን የመልመጃ ጥያቄዎች ካጠናቀቅህ በኋላ መልሶችህን ከተሰጡት መልሶች ጋር አመሳክረህ ትክክል ያልሆንከውን አስተካክል።
3. በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና ከወሰድህ በኋላ መልስህን በጥንቃቄ አስተያይ። በትክክል ያልመለስካቸው ጥያቄዎች ካሉም አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

ኢየሱስን ወደ መምሰል ማደግ

ዓላማ 1 ለመንፈሳዊ እድገት ምሳሌአችንን ለይቶ ለማወቅ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አማኙ እንደገና የተወለደው ከአዲስ ቤተሰብ ነው። በውስጡ አዲስ የተወለደው መንፈስ ወይም ዘር የእግዚአብሔርን አምሳል የያዘ ነው። ቤተሰቡን እየመሰለ እንደሚያድግ ሕፃን፥ አማኙም እግዚአብሔርን እየመሰለ ማደግ ይገባዋል። ያም የእግዚአብሔር አምሳል በኢየሱስ ክርስቶስ ገጽታ ላይ የታየ ሲሆን፣ ኢየሱስ በሰው አምሳል የኖረ አምላክ እንደነበረ በግልጽ የሚያስረዳ ነው። ለእያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ እድገት ዋና ምሳሌ ሆነ።

ግቡን መመልከት

ዓላማ 2 ከፊልና ፍጹም ሙሉ በሆነ መንፈሳዊ እድገት መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ።

የመንፈሳዊ እድገታችን ግብ ምን እንደሆነ በግልጽ ለመረዳት እንድንችል በሮሜ 8:29-30 ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚናገረውን ማወቁ ጠቃሚ ነው። በዚህ ክፍል እንዲህ ይላል፦ "የእግዚአብሔር ልጅ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር እንዲሆን፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ ስለ ወሰነ ነው። አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፣ የጠራቸውንም አጸደቃቸው፣ ያጸደቃቸውንም አከበራቸው" በማለት ይናገራል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባጠናናቸው ተከታታይ ትምህርቶች አማኝነት የእግዚአብሔርን ልጅ መምሰል ማለት ምን እንደሆነ ለመረዳት ችለናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት የምናቀርበው ለመንፈሳዊ እድገት ከሁሉም በላይ ከፍተኛ የሆነውን ግስረጃ ሲሆን፣ ይኸውም የኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርይ በጠባያችንና በኑሮአችን ማንጸባረቅ ነው።

ወደፊት እየተጓዝን የምንሄድበት ግብ ዋና መግለጫ የሆነው ሊላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ በኤፌ 4:13 ላይ የሚገኘው ሲሆን፥ ቃሉም እንዲህ ይላል፦ "እንዲሁም የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርስን፥ ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ እንደሆነው እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው።" በማለት ያስረዳል።

ሙሉ ሰው ለመሆን ወይም በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰለ ሰው ለመሆን ዋናው ወሳኙ "የእግዚአብሔርን ልጅ ማወቅ" እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይነግረናል። ሦስት መሠረታዊ የእውቀት ደረጃዎች እንዳሉም መረዳት እንችላለን። የመጀመሪያው ከዚህ በፊት ተገናኝተን ስለማናውቀው ሰው በመረጃ ብቻ ስለ እርሱ ማወቅ መቻል ሲሆን፣ አንድን ሰው በተሻለ መንገድ ልናውቀው የምንችለው ደግሞ ከእርሱ ጋር ተገናኝተን በመተዋወቅ ነው። በሦስተኛ ደረጃና ከሁሉም በዘለለ መንገድ የቅርብ ጓደኛችንን እንደምናውቀው በቅርበት ልናውቀው እንችላለን።

(1). በፊልጵ 3:10 ላይ ጳውሎስ ከሦስቱ የእውቀት ደረጃዎች የጠቀሰው የትኛውን ነው? (ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጳውሎስ የጻፈው ወደ ሕይወቱና አገልግሎቱ ፍጻሜ አካባቢ በእስር ቤት ሳለ መሆኑን በማስታወስ መልሱን በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

የጳውሎስ የልብ ጥማት የእኛንም ክርስቶስን በቅርበት በማወቅና እርሱን በመምሰል በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን ለመሄድ ያለንን ምኞት ሊያነቃቃ የሚችል ነው። ለመንፈሳዊ እድገታችን ይረዳን ዘንድ ክርስቶስን በጣም በቅርበት ለማወቅ መሻት አለብን።

ጳውሎስ ከእድገት ጋር በመንዝ እድገትን ያለማቋረጥ ዓላማውና ግቡ በማድረግ ለመኖር ፈቃደኛ ነበር። በፊልጵ 3:12 ላይ እንደገለጠው፦ "አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንሁ እያደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝኩበትን ያን ደግሞ እያዝለሁ ብዬ እፈጥናለሁ።" በማለት ይናገራል። ትንሽ ዝቅ ብሎ በፊልጵ 3:15 ላይ ደግሞ ራሱን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሙሉ ሰው ከሆኑት ወይም ከበሰሉት ጋር በመቁጠር ሊናገር፦ "እንግዲህ በመንፈሳዊ ሕይወት የጠነከርን ሁሉ ይህን የመሰለ አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል፣ የምትለያዩበት ሃሳብ ከመካከላችሁ ቢኖር፣ ይህንንም ሃሳብ እግዚአብሔር ግልጥ ያደርግላችኋል" ይላል።

እኛን የሚያበረታታ ሆኖ የምናገኘው ሐዋርያው ጳውሎስ በአንድ መንገድ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ፍጹም ወደ መሆን ደረጃ መድረሱን ይናገርና በሌላ

በኩል ደግሞ ወደዚህ ፍጹምነት ደረጃ ገና እንዳልደረሰ ይናገራል። ዮሐንስ የዘሰሰ የስባት ዓመት ልጅ ነው ብሎን ስለ አንድ ልጅ ብንናገር ከስባት ዓመት ልጆች ጋር ሲመዛዘን የተሻለ ብስለት የሚያሳይ ነው ማለታችን ነው። የሰባት ዓመቱ ከሃያ ዓመቶች ጋር ሊመዛዘን አይችልም። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደሚዛነን እያደግን የበሰልን ሰዎች ለመሆን እንደምንችል በመገንዘብ፣ ክርስቶስን ወደ መምሰል ወደ ጠቅላላው ግብ ሙሉ በሙሉ ለመሥጣት በሙሉ ልባችን መሻትን ማቋረጥ የለብንም።

የክርስቶስ ሕይወት መለያ ባሕርያት

ዓላማ 3 የክርስቶስን ባሕርይ ለይቶ ለማወቅ።

ዓላማችን ወይም ግባችን ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል ነው ብለናል። እግዚአብሔር እኛ ልጁን እንድንመስል ይፈልጋል። እርሱን መምሰል ማለት ምን እንደሆነ ለማወቅ እንችላለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሰዎች መካከል ኖሮአል። እያደገ፣ እየተማረና እየጠነከረ መሄዱን በሉቃ 2:52 ላይ የተጻፈው ቃል ሲገልጽ፦ "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር" ይላል። የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወቱ ለመፈጸም ሲል ደግሞ የአገልጋይን ስፍራ በመቀበል እንዳገለገለ ቀደም ሲል ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ዓላማችን ኢየሱስ በባሕርዩ ምን እንደነበር ለማየት በመሆኑ፦ ባሕርይ ማለት "ከሌሎች ተለይተን የምንታወቅበት ጠባይ" መሆኑን አስቀድሞ መረዳቱ አስፈላጊ ነው።

በቃላትም ሆነ በድርጊት የሰውን ባሕርይ ስንመለከት ትክክለኛ ማንነቱን ማወቅ እንችላለን። የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሁሉ መሠረታዊ ባሕርያት አሉአቸው። የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ከተለያዩ አገሮች የመጡና የተለያየ የቆዳ መልክ ቢኖራቸውም፣ እውነተኛ ክርስቲያኖች በውጭ ሰዎች ሲጠኑ ሁሉም የሚያሳዩት አንድ ዓይነት ባህሪይ አላቸው። ይህም የሚያረጋግጠው ሁሉም የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆናቸውን ነው።

የኢየሱስን ባሕርይ በሰፊው ለማጥናት የሕይወት ዘመን ጥረት የሚጠይቅ ነው። ለአሁኑ ጥናታችን እንዲረዳን የባሕርዩን መሠረታዊና ዋና ሁኔታዎችን ማወቁ ስለሚረዳ፣ በኢየሱስ የምናየው የመጀመሪያው ባሕርይ ራሱን ባዶ በማድረግ ራስ ወዳድነትን አስወግዶ መኖሩ ነው። ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ያኖረው ለአባቱ ክብር እንደሆነ በዮሐ 1:14 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ፦ "ቃልም ሥጋ ሆነ፣ አጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ እንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን" በማለት ይናገራል። ሰዎች ክርስቶስን በሚያዩበት ጊዜ በእርሱ የሚያዩት የአባቱን ክብር ነው።

(2). በዮሐ 14:8 ላይ ጌታ ሆይ፣ አብን አሳየንና ያዘቃናል በማለት ፊልጶስ ኢየሱስን በጠየቀው ጊዜ ኢየሱስ፦ "እኔን ያየ አብን አይቶአል"

በማለት መለሰ። በዮሐ 14:10 ላይ ኢየሱስ ስለ ቃሉና ስለሥራው ምን ተናገረ?

(3). በዕብ 1:3 ላይ ኢየሱስ የተገለጸው ምን እንደሚያንጸባርቅ ሆኖ ነው?

ሀ. የተውሶ ባሕርይ
ለ. ምድራዊ ክብር
ሐ. የእግዚአብሔርን ክብር

በዕብ 1:3 ላይ ኢየሱስ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ነው። እርኩስ መናፍስት እንኳ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለይተው ያውቁ ነበር። (ማቴ 8:29፣ ማር 1:24፣ 3:11 እና ሉቃ 4:41 ተመልከት)።

(4). በሐዋ 19:11-16 ላይ የተጻፈው የሚያመለክተው ዕርኩሳን መናፍስት በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ እግዚአብሔርን እንዳዩ ነው። ሰው ብቻ በሆነ፣ እግዚአብሔርን የመምሰል ባህሪይ በነበረው በአንድ በሌላ አስተማሪ ውስጥ እግዚአብሔርን አይተውታል። ዕርኩሳን መናፍስት እግዚአብሔርን በውስጡ ያዩት ይህ ሰው ማን ነበር?

ኢየሱስ ራስ ወዳድ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለኛ ምሳሌ የሚሆኑን ሌላም ሁለት ዋና ባሕርያት ነበሩት። ሁለቱም ባሕርያት የተገለጹት በፊልጵ 2 ላይ ሲሆን በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ በራሱ ላይ የለውን መልክ ብቻ ሳይሆን በፈቃዱ የወሰደው የአገልጋይንም መልክ ነበር።

(5). በፊልጵ 2:5-11 ላይ የተጻፈውን ካነበብክ በኋላ በቁ. 8 ላይ የተገለጸውን ሁለት ባሕርያት የሚያሳየውን ፊደል ክበብ።

ሀ. ቸርነትና መልካምነት	ሐ. ደስታና ፍቅር
ለ. የዋህነትና ታጋሽነት	መ. ትህትናና ታዛዥነት

እነዚህ የክርስቶስ ባሕርያት በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ በግልጽ ይታዩ ነበር። ብዙዎቹን የክርስቶስ ባሕርያት የምናገኛቸው ግን በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ባልሆነ መንገድ ነው። ስለ ክርስቶስ ባሕርይ ስናጠና የፍቅር፣ የደስታ፣ የሰላም፣ የትዕግሥት፣ የቸርነት፣ የበጎነት፣ የታማኝነት፣ የትህትናና ራስን የመ ገዛት ባሕርይ እንዳለው እናያለን።

(6). በዮሐ 8:1-11 ስለ ኢየሱስ የተጻፈውን ካነበብክ በኋላ በዚህ ታሪክ ውስጥ የሚገኙትን ሦስቱን የኢየሱስን ባሕርያት ዘርዝር።

የዘረዘርናቸው ባሕርያት "የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ" ተብለው ይጠራሉ እነዚህን ፍሬዎች በሕይወታችን ለማፍራት የምንችለው በሰብአዊ ባሕሪያችን ሳይሆን ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ስናስገዛ ነው። እነርሱም

እግዚአብሔር ሰዓለም ራሱን የሚገልጥበት እንደ ነፍሳችን መነፈቻ መስኮቶች ናቸው። ኢየሱስ እግዚአብሔርን ሰዓለም ለማሳየት የሰብአዊ መንፈሱን መስኮቶች ሁሉ ነፍት አድርጎ ነበር።

እንደ ኢየሱስ መመላለስ

ዓላማ 4 እንደ ኢየሱስ ለመሆን ለአማኙ ለምን አስቸጋሪ እንደሆነ ለመግለጽ።

እንደ ኢየሱስ መሆን ተፈጥሮአዊ ደግሞም አዲስች ነው። ተፈጥሮአዊ የሆነበት ምክንያት በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በተወሰድን ጊዜ የእግዚአብሔር ዘር ወይም ባሕርይ በውስጣችን ስለሚኖር ነው። ይህ ዘር በውስጣችን እያደገ ሲሄድ የእግዚአብሔርን አምሳል ያሳያል። ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 1:5 ላይ ይህንን እውነት ሲገልጽ፦ "በዐን ፈቃዱ እንደ ወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን" ይላል። አስቸጋሪ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ በገላ 5:17 ላይ ሲገልጽ፦ "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም" ይላል።

የፈቃድ ምርጫ

ዓላማ 5 አማኙ ኢየሱስን ለመምሰል እንደሚችል ለመግለጽ።

በፊልጵ 2:7 ላይ ስለ ኢየሱስ ባሕርይ ሲናገር፦ "ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ, ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ" ይላል። የሰው መንፈስና ፈቃድ የሰው ክፍተኛው ስጦታ ነው። እግዚአብሔርን የመምሰል ዘር በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ቢኖርም የእግዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ እንዲያበራ መወሰን ያለበት አማኙ ነው። አማኙ ይህንን ውሳኔ እንዴት እንደሚያደርግ በኤፌ 3:16 እና 19 ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጸለቅ ያለ ማብራሪያ ሲሰጥ፦ "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ፣ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፣ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፣ . . . ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፣ እስከ እግዚአብሔርም ሩጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ" ይላል።

(7). በኤፌ 3:14-19 ላይ የተጻፈውን ካነበብክ በኋላ እንዳንድ *የለውን ፈቃድ* ውሳኔ የሚጠይቁትን ሐረጎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር። ለምሳሌ, የመጀመሪያው በቁ. 16 ላይ፦ "በኃይል እንድትጠነክሩ" የሚለው ነው።

በሐረጎቹ የተዘረዘሩት ሁሉ የእኛ ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም ሊከናወን የሚችለው ግን እንደ አማኙ ምርጫ ነው። በኤፌ 4:1 ላይ ደግሞ ዋናውን ጉዳይ ሲያቀርብ፦ "እንግዲህ በጌታ አስር የሆንኩ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ" በማለት ይናገራል።

(8). የክርስትና ሕይወት ዓላማና መመዘኛ ስላለው እያንዳንዱ አማኝ በተሰጠው መመዘኛና በተሰጠው ደረጃ መሠረት ለመናር መወሰን አለበት። በኤፌ 4:13 ላይ በተጻፈው መሠረት ያ የተፈለገው መመዘኛ ምንድን ነው?

(9). በኤፌ 4:2 ላይ በሕይወታችን እንድናሳይ የተጠየቅነው ቢያንስ አምስት ባሕርያት ተጠቅሰዋል። እነዚህም ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት ምልክቶች ናቸው። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጠቀሱትን አምስቱን ከምርጫዎቹ በማክበብ አመልክት።

ሀ. መታገሥ	ሠ. ገርነት	ቀ. የዋህነት
ለ. ቸርነት	ረ. ትዕግሥት	በ. ቻይነት
ሐ. ፍቅር	ሰ. ትህትና	
መ. ሰላም	ሸ. ደስታ	

አማኙ በውስጡ ለማንጸባረቅ የሚፈቅደውን ባሕርይ የሚወስነው የአማኙ ፈቃድ መሆኑን በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። ጊዜ ሲኖርህ፥ የኤፌሶንን መጽሐፍ ጥቅስ በጥቅስ ብትመለከት ሰሰው ፈቃድ ምን ያህል ጊዜ ልመና እንደቀረበ ለመገንዘብ ትችላለህ። በኤፌ 4:24 ላይ፦ "አዲሱን ሰው ልበሱ" የሚል ትእዛዝ ያስተላልፍልናል፤ በ5:15 ላይ ደግሞ "እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ" በማለት፤ በኤፌ 6:11 ላይ "የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ" በማለት መመሪያ ማስተላለፉን ይቀጥላል። ለዚህ ጥናት የሚረዳን እግዚአብሔር መመሪያውን እንደሚሰጥ የሚያሳየንንና እኛ ደግሞ የክርስቶስን ባሕርይ በሕይወታችን ለማንጸባረቅ አንድ ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን እንደሚገባን የሚያሳየንን አንድ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንመለከታለን። በ2ጴጥ 1:3-8 ላይ የተጻፈው ስለዚሁ ሲገልጽ እንደዚህ ይላል፦

የመለኮቱ ኃይል፥ በጣዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፣ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን። ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፣ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል

የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና፤

(10). ከዚህ ምንባብ ውስጥ ክርስቲያን የሚለማመዳቸውን ስንት ባሕርያት መቁጠር ትችላለህ?

ሀ. 8 ለ. 4 ሐ. 12 መ. 20

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ አማኙ እነዚህን መልካም ባሕርያት በሕይወቱ ላይ የመጨመር ሃላፊነት አለበት። እግዚአብሔር "ውድ የሆኑ ስጦታዎችን"ና "መለኮታዊ ተፈጥሮ" ሰጥቶናል። *እግዚአብሔርን የመምሰል ኃይል የምናገኘው በአዲስ ልደታችንና በነፃ ፈቃዳችን በመሆኑ ኢየሱስን የምንመስል እንድንሆን አንድ ነገር ማድረግ ይገባናል።*


የእግዚአብሔር ስጦታና የእኛ ሥራ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ሲካካስ እናየዋለን። በፊልጵ 2:12-13 ላይ ስለዚሁ ሲገልጽ፦ "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፣ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" ይላል።

ደኅንነት፥ ሙሉ መሆን፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ያለውን እቅድ መፈጸም ተብሎ ሊገለጽ ይቻላል። እኛ መሥራት አለብን፣ እግዚአብሔር ደግሞ እኛን ለማሰራት ፈቃደኞች እንድንሆንና ችሎታ እንዲኖረን ማድረግ አለበት። ስለዚህ አስደናቂ ለሆነው ሚዛናዊ ሥራ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

ለመንፈስ ቅዱስ ራስን ማስገዛት

ዓላማ 6 አማኙ ለመንፈስ ቅዱስ ራሱን አሳልፎ መስጠቱንና ኢየሱስን ከመምሰሉ ጋር ለማዛመድ።

በክፍለ ትምህርት 4 እና 6 ላይ ስለመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መማራችን የሚታወስ ነው። ጌታ ኢየሱስ የሕይወቱን ዓላማ እንዲፈጽም ያስቻለው መንፈስ ቅዱስ ነበር። ኢየሱስ በመንፈስ እንደተመራና እንደተቀባ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። የኢየሱስ መልካም ባሕርይ የእኛ ሊሆን የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ሲቆጣጠር ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በገላ 5:25 ላይ ስለዚሁ ሲጽፍ፦ "በመንፈስ የምንኖር ከሆንን፥ በመንፈስ እንመራ" በማለት ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ የአማኙን ሕይወት ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠር ያን ጊዜ አማኙ የክርስቶስን ባሕርይ በውስጡ ሊያፈራ ይችላል። በገላ 5:22-23 ላይ የክርስቲያን ባሕርይ የሚታዩበት መስኮቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።



(11). በኤፌ 5:18 ላይ የተሰጠንን ትዕዛዝ ጻፉ።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን ማለት እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። *የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር በይበልጥ ስንፈቅድለት በባሕሪያችንና በኑሮአችን በይበልጥ ኢየሱስን እየመሰልን እንሄዳለን።* ጊዜ ሲኖርህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን እንብብና ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ የሚላቸውን ቦታዎች ሁሉ አስምርባቸው።

የእኔነር ዘይቤ

ዓላማ 7 ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ በሚያስገዙ አማኞች ውስጥ መንፈሳዊ እድገትን የሚያስገኘው ማን እንደሆነ ለመግለጽ።

አንድ ቀን ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጣና በዚያ የተሰበሰቡትን ሰዎች ለማስተማር ተቀመጠ (ማቴ 5:1-2)። በዚህም ስፍራ የሰጠው ትምህርት "የተራራው ስብከት" እየተባለ ይጠራል። በዚህም በተራራው ስብከት ላይ ብጹአን የተባሉ አሜሜር መግለሜዎች አሉ። ብጹአን ማለት "ከሁሉም በላይ ደስተኛ" ወይም የተባረኩ ማለት ነው። በነዚህ አሜሜር መግለሜዎች ኢየሱስ የገለጠው እውነተኛ ደስታን ስለሚያስገኝ የኑሮ ዓይነት ነበር።

በማቴ 5:3-10 ላይ እያንዳንዱ ብጹአን የተባለው አሜር መግለሜ የሚያስረዳው መንፈስ ቅዱስ በሚፈቅዳለት አማኞች ውስጥ የሚያስገኘውን ልባዊ ዝንባሌና ባሕርይ ነው። እርሱ የሚያስገኘውም መልካም የልብ ዝንባሌና ባሕርይ መንፈሳዊ እድገትን ያስገኛል። ለመንፈስ ቅዱስ ምን ያህል ሙሉ በሙሉ እንደተሰጠን ራሳችንን ለመመርመር እንዲረዳን "ብጹአን ናቸው" እያለ የተናገረውን በእሜሩ ብንመለከተው መልካም ነው።

በቁ. 3 ላይ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብዑዓን ናቸው" ይላል። መንፈስ ቅዱስ የእኛን ችግርና የጎደለንን ነገር ዘወትር እንድናውቅ ይረዳናል። ይህም በእግዚአብሔር ላይ የመደገፍ ሁኔታን በማስከተል ከፍተኛ ዋጋን እንድናገኝ ይረዳናል።

በቁ. 4 ላይ "የሚያዝኑ ብሁዓን ናቸው" ይላል። ይህ የሚያመልክተው ክርስቶስ በሕይወታችን እንዳያከብር ስለሚያደርጉ ማንኛውም ነገሮች የልብ ሃዘን ሁኔታን ለመግለጽ ነው። ንስሐ በመግባትና ኃጢአትን በመናዘዝ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሃዘን ነው።

በቁ. 5 ላይ "የዋሃች ብሁዓን ናቸው" ይላል። የኢየሱስ ባሕርይና ዝንባሌ ራሱ የሚያሳየው የዋህነትንና ራስን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት ነው። የክርስቶስ አገልጋይ በሆነ ሁሉ ከሁሉም ይበልጥ ከቀላሉ የሚታየው "የዋህነት" ነው።

በቁ. 6 ላይ "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብሁዓን ናቸው" ይላል። ይህ ከልብ የሆነ መታዘዝን የሚያመለክት ነው። ልክ ኢየሱስ እንዳለው፥ እማኙም፣ "እምላኬ ሆይ፣ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ" ማለት አለበት (ዕብ 10፡7)።

በቁ. 7 ላይ "የሚምሩ ብሁዓን ናቸው" ይላል። ይህ ይቅርታ የማድረግና የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚያመለክት ባሕርይ ነው። ይህ ባሕርይ ክለ መራርነትንና ቅያሜን በልብ እሸሩ ማለት አይቻልም። ይህም የክርስቶስን ሕይወት በግልጽ የሚያሳይ ነው።

በቁ. 8 ላይ "ልበ ንጹሖች ብሁዓን ናቸው" ይላል። የውስጥ ልባችን በራሳችን ፍላጎት ክልተያዘ፣ ስለ ኢየሱስ እውነተኛነት የሚናገረን ራዕይ ከፍ ያለ ይሆናል።

በቁ. 9 ላይ "የሚያስተራርቁ ብሁዓን ናቸው" ይላል። እዚህ ላይ የምናየው ባሕርይ ለሌሎች የማስጠን፣ የማክፈልንና ለሌሎች የመራራትን መንፈስ ነው።

በቁ. 10 ላይ "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብሁዓን ናቸው" ይላል። ይህ ደግሞ በሁሉ ነገር ደስ ሊለን እንደሚገባ የሚያመለክት ነው። እማኙ በማንኛውም ደረጃና ልምምድ የእግዚአብሔርን የፍቅር እጆችና እንክብካቤ ለይቶ የሚያቅበት እዚህ ላይ ነው።

(12). በማቴ 5፡3-10 ላይ የተጻፈውን እንደገና ክነበብክ በኋላ ብሁዓን ለተባሉት ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚባርካቸው የሚናገረውን መግለጫ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፍ። ለምሳሌ ቁ. 3 ላይ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብሁዓን ናቸው" ካለ በኋላ ምን ዋጋ እንደሚቀበሉ ሲናገር፦ "መንግሥተ ለማያት የእነርሱ ናትና" ይላል።

እንድ ሰው የበለለ ክርስቲያን መሆኑን ከሁሉም በላይ የሚያረጋግጠው ማስረጃ የኢየሱስ ባሕርይ በሕይወቱ ሲታይ ነው። አማኞች በመጀመሪያ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩት በአንጾኪያ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋ 11፡26 ላይ ይነግረናል። ከዚያን ጊዜ በፊት ለረጅም ዓመታት "የመንገዱ

ስዎች" ተብለው ነበር የሚታወቁት። አንጾኪያ በዓለም የታወቀች የባርያ መናኸሪያ ከተማ ነበረች። በዚያ ጊዜ አንድ ባሪያ የጌታው የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ስም ፊደል እክሉ በመጠራት የሚን ባሪያ እንደሆነ ተለይቶ ይታወቅ ነበር። ምናልባት የሚያምሩ ስዎች እነዚህን አማኞችን "እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች" እድርገው አያተዋቸው ይሆናል። ክርስቲያን ብለውም ጠሩአቸው። ይህ እውነት ያሁን አያሁን ባያታወቅም፣ ክርስቲያን ተብሎ የመጠራትን ያህል የዘለለ ክብር የለም። ክርስቲያን የሚለው ቃል የሚጠቅሰው የክርስቶስን አገልጋዮች እንደሆነ እናውቃለን። የእርሱን ባሕርይ ለመያዝና እርሱን ለመምሰል የተሰማሙ ማለት ነው።

መከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት። መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" የሚሉትን ፈደሎች በመጻፍ መልሱን ስጥ።

1. ማስረጃ ማለት መረጃዎችን የሚያቀርብ ነው።

2. ለመንፈሳዊ እድገት የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አስፈላጊ ነው።

3. ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደ ተሳካለትና ፍጹም እድገት ላይ እንደደረሰ ተናገረ።

4. ባዘሪያ ከሌሎች የሚለየን አስፈላጊ የሆነ ተፈጥሮአችን ነው።

5. በተራራው ስብከት ላይ "ብሁኑን ናቸው" እያለ ጌታ ኢየሱስ የሰጠው አጭር ትምህርት መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ የሚያስገኘውን የልብ ዝንባሌና ባሕርይ የሚገልጥ ነው።

አጭር መልስ። ስጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ጻፍ።

6. በገላ 5:22-23 ላይ በተጻፉት የመንፈስ ፍሬዎች አጠገብ ምልክት እድርግባቸው።

ሀ. ዘንድ	ረ. ትዕግሥት	ተ. የውሃት
ለ. ተዓምራት	ሰ. ቸርነት	ቸ. ራስን መግዛት
ሐ. ሰላም	ሸ. እምነት	ኀ. ፍቅር
መ. ህልውና	ቀ. ፈውስ	ነ. ጥበብ
ሠ. ልሳን	በ. ታማኝነት	ኘ. ደስታ

7. የመንፈሳዊ እድገታችን ማስረጃው የክርስቶስ ባሕርይ በሕይወታችን መገለጥ ሲሆን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ባሕርያት ራስህን ለመገምገም ሞክር። መንካራ ከሆነ ከጎኑ "ጠ" ጻፍ፥ መካከለኛ ከሆነ ከጎኑ "መ" ጻፍ፥ ደካማ ከሆነ ከጎኑ "ደ" ጻፍ፥ ምንም እድገት ያላሳየ ከሆነ ከጎኑ "ም" በመጻፍ አመልክት።

ባሕርያት	ጠ	መ	ደ	ም
ፍቅር				
ደስታ				
ሰላም				
ትዕግሥት				
ቸርነት				
በጎነት				
ታማኝነት				
የዋህነት				
ራስን መግዛት				
እውቀት				
እግዚአብሔርን መምሰል				

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ጳውሎስ የጠቀሰው ሦስተኛውን ወይም በቅርበት ደረጃ ማወቁን ነው። እርሱ ስለ ኢየሱስ እውነቱን አውቋል (ገላ 1:6-10)። እርሱ በግል ልምምዱ ክርስቶስን አውቋል (የሐዋ 9:1-19)። ጌታን በቅርበት የማወቅ ፍላጎት ግን የሕይወት ዘመን ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ይህም ሙሉ በሙሉ ሊፈጸም የሚችለው በጌታ ፊት ከእርሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር በምንገናኝበት ጊዜ ብቻ ነው።

7. በእምነት (ቁ 17)። የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ (ቁ 17)። ለማስተዋል (ቁ. 18)። የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ (ቁ. 19)።

2. ከአባቱ ዘንድ እንደመጡ

8. የክርስቶስ ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ

3. ሐ

9. ሀ. መታገሥ ሠ. ገርነት ቀ. የዋህነት
ሐ. ፍቅር ረ. ትዕግሥት

4. ጳውሎስ

10. ሀ

5. መ

11. በመንፈስ ተሞሉ።

6. ችርነት፣ ፍቅርና ጨዋነት (ሌሎችም ባሕርያት እዚህ ላይ ሊገኝ ይችላሉ)።

12. ቁ. 3፡ *መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።*
ቁ. 4፡ *መጽናናትን ያገኛሉና።*
ቁ. 5፡ *ምድርን ይወርሳሉና።*
ቁ. 6፡ *ይጠግባሉና።*
ቁ. 7፡ *ይማራሉና።*
ቁ. 8፡ እግዚአብሔርን *ያዩታልና።*
ቁ. 9፡ የእግዚአብሔር ልጆች *ይባላሉና።*
ቁ. 10፡ *መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።*

9 የጠቃሚ አገልግሎት ማስረጃ

ትምህርት

መንፈሳዊ ብስለት የተለመደ የእድገት ሂደት መሆኑን ተመልክተናል። በውስጥና በውጪ የአማኙ የእድገት ጠላት በሆኑት እድገቱ ሊሰናከልና ሊቆም ቢችልም፣ አማኙን ወደ ብስለት ለማምጣት የሚረዱ ታላቅና ግሩም የሆኑ ነገሮች አሉ። በ1ዮሐ 4:4 ላይ "... በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" በማለት ይገልጻል።

ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላል እየተንቀሳቀሰ ባለው አማኝ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ልዩ ማስረጃዎች አሉ። በመጀመሪያ በማያሳስት መንገድ ቤተሰቡን መስሉ ይወጣል። በልማዱና በዝንባሌው የኢየሱስን ባሕርይ በደብልተ እያሳየ *ሰ*ማማት ይጀምራል። ዓለም ቤተ ክርስቲያንን፡ "ክርስቶስን ማየት እንወዳለን" ብላ ትጠይቃለች (ዮሐ 12:21)። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለው አማኝ ለዓለም መልስ ይሆንላታል። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ያሉ ወንዶችና ሴቶች የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወትና ኢየሱስን መምሰል ማለት ምን እንደሆነ ያገለግላሉ። ዓለምም ኢየሱስን በአማኞች ውስጥ ለማየት ትችላለች።

በመንፈሳዊ ሕይወት ለመብሰሉ ሁለተኛው ግልጽ የሆነ ማስረጃ የአማኙ ሥራ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ የሚሄድ አማኝ ጠቃሚ የሆነ ክርስቲያን ነው። እድገቱ እየጨመረ ሲሄድ አማኙ የበለጠ ሃላፊነት መቀበል የሚችል ይሆናል። በክርስቲያን አገልግሎት ውስጥም በሚሰጠው ሥራ ጠቃሚና የበለጠ አስፈላጊ እየሆነ ይመጣል። የወላጆች አንደኛው ትልቁ ደስታቸው ልጃቸው ጠቃሚ ወደ መሆን ደረጃ እያደገ ሲሄድ ማየት ነው። ልጃቸው የመጀመሪያ ተግባሩንና ሃላፊነቱን ተቀብሎ በአግባቡ ሲያከናውን ሲያዩ በደስታ ስሜት ልባቸው ይነካል። የሚያድግ ሰው ሃላፊነት ሊወስድና ጠቃሚ ሲሆን የከፍተኛ መሳካት ውጤት ሦስክት ነው። የመንፈሳዊ ብስለትም እውነተኛው ማስረጃ ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት ማበርከት ነው።

የክፍለ ትምህርቱ አክፋፈል

- የክርስቶስ አገልግሎት
- የአማኙ አገልግሎት
- ማጠቃለያ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የኢየሱስን ጠቃሚ አገልግሎት በይበልጥ መገንዘብ መቻል።
- የኢየሱስን አገልግሎት ከአማኙ አገልግሎት ጋር ማገናዘብ መቻል።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ዘጠነኛውን ክፍለ ትምህርት በጥንቃቄ አንብብ።
2. በትምህርቱ ማጠናከሪያ ላይ የተሰጡትን መልመጃዎች በጥንቃቄ ከሰራህ በኋላ በመጽሐፉ ውስጥ ከተሰጡት መልሶች ጋር አገናዝብ።
3. በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና ከወሰድህ በኋላ መልሶችህን በጥንቃቄ አረጋግጥ፣ በትክክል ያልመለስካቸውን ጥያቄዎች እንደገና በመከለስ አስተካክላቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር

በመሠረቱ እግዚአብሔር ለሰው ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት ሰጥቶአል። ቀደም ሲል ሰውን በኤደን ገነት የተመለከትነው ጠቃሚ በመሆን ሲሠራ ነው። በዘፍ 2:15 ላይ፦ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው" ይላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር የሚታየውን ዓለም ሲፈጥርና በውስጥዋም ሲሠራ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ተናገረ፡ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፣ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንሰሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ" በማለት በዘፍ 1:26 ላይ ተናገረ። ከዚህም በላይ ሰዎች በምድር ላይ ሁሉ እንዲኖሩና በቁጥራቸው ሰር እንዲያደርጉአት ዘፍ 1:28 ላይ ሲገልጽ፦ "በምድር ላይ የበላይነትን ሰጠሁህ" በማለት ተናገረ። እዚህ ላይ በመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት ላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር በሰራው ሥራ ሁሉ እንደተደሰተ ለመናገር ቻለ።

ከዚያም ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ሰው በእግዚአብሔር የተሰጠውን አገልግሎት እንዳይፈጽም ኃጢአት ጣልቃ ገባ። በዚህም ምክንያት ሰው በምድር ላይ ከተሰጠው ሥልጣን ተሽሮ ከኤደን ገነት ተባረረ። ቢሆንም ግን አሁንም ሰው የሚያከናውነው ሥራ ነበር። በዘፍ 3 17-19 ላይ፦ "ምድር በቂ ምግብ ትሰጥ ዘንድ፣ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ በልፋትና በጥረት እንጀራህን ትበላለህ፣ ምድር ፍሬዋን ትሰጥ ዘንድ በፊትህ ወዝ ጥረህ ግረህ ትሠራለህ" ይላል።

ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከኃጢአት ሊድን በመቻሉ የእግዚአብሔር ስም የተመለሰ ይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም እግዚአብሔር ያቀደለትን ጠቃሚ ሥራዎች እንደገና መሥራት ይችላል። ለጠቃሚ አገልግሎታችን ምሳሌያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው።

የክርስቶስ አገልግሎት

የክርስቶስ ምሳሌነት

ዓላማ 1 መጥምቁ ዮሐንስ ከሰጠው ምስክርነት የበለጠ በኢየሱስ ስም የተሰጠውን ምስክርነት ለመግለጽ።

ሉቃስ "የሐዋርያት ሥራ" የተባለውን ሁለተኛውን መጽሐፉን ሲጀምር፦ "ኢየሱስ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ያደረገውንና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ የመጀመሪያውን ነገር እንደጻፈ ይናገራል" (ሐዋ 1:1)። በኋላም በሁለተኛው መጽሐፉ ላይ ሉቃስ በኢየሱስ ሥራ ላይ በማተኮር፦ "እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ" በማለት በሐዋ 10:38 ላይ ይናገራል።

ቀደም ሲል በአገልግሎቱ ኢየሱስ አንድ ሽባ ሰው በሰንበት ቀን ፈውሶ ነበር። ከዚያም የአይሁድ ባለሥልጣኖች በሰንበት ቀን ይህን በማድረጉ ሊወግሩት ተነሡ። በዚህን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐ 5:17 ላይ፦ "አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ" ብሎ መለሰላቸው። ይህ የኢየሱስ ሥራ ጠቃሚ እንደሆነ የሚያሳይ ልዩ ምሳሌ ነው።

(1). በዮሐ 5:36 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት መጥምቁ ዮሐንስ ከሰጠው ምስክርነት ይበልጥ ለኢየሱስ የተሰጠው ምስክርነት ምንድነው?

ሀ. የኢየሱስ ታምራዊ ኃይል
ለ. የኢየሱስ ማንኛውንም ሰዎችን መቀበል
ሐ. የኢየሱስ ሥራዎች

(2). በዮሐ 9:4 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ከዚህ በታች ያሉትን ሁለት ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. ኢየሱስ ሥራው ለምን ያህል ጊዜ መቀጠል እንዳለበት ተናገረ?
ለ. ሥራውስ መቼ እንደሚቆም ኢየሱስ ተናገረ?

የእግዚአብሔር አብ ክብር

ዓላማ 2 በኢየሱስ ሥራና በአባቱ ክብር መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ።

ኢየሱስ ከአባቱ ፈቃድ ውጭ ምንም ማድረግ አይፈልግም ነበር። ሕይወቱን በሙሉ የኖረው የአባቱን ዓላማ ለማከናወን በመሆኑ በዮሐ 4:34 ላይ፦ "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ እደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው" በማለት ተናገረ። ሥራው፣ ሕይወቱና የተናገራቸው ቃላት ሁሉ ከአባቱ እንደሆኑ በይፋ ለሰው ሁሉ ተናገረ። በምድራዊ ሕይወቱም መጨረሻ፥ በዮሐ 17:4 ላይ፦ "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ" በማለት ለአባቱ ተናገረ።

(3). በዮሐ 10:25 ላይ ኢየሱስ በተናገረው መሠረት እርሱን በመወከል የሚናገረው ምንድን ነው?

(4). በዮሐ 17:4 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት የኢየሱስ ሥራ ለአብ ክብር የሚያመጣው ለምንድን ነው?

የአማኞች አገልግሎት

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የአማኙ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት የሚለካው በኢየሱስ ሙላት ነው። አንደኛው ግልጽ የሆነ መለኪያ የኢየሱስ ባሕርይ በአማኙ ውስጥ መታየት ሲሆን፥ ሌላው የመንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ማስረጃ ደግሞ አማኙ በመንፈስ ቅዱስ በኩል የኢየሱስን አገልግሎት ሲያከናውን ነው።

የኢየሱስን አገልግሎት መፈጸም

ዓላማ 3 አሁን በዓለም ላይ የኢየሱስ አገልግሎት እንዴት በመፈጸም ላይ እንደሆነ ለመግለጽ።

በዮሐ 14:12-14 ላይ ኢየሱስ ስለ አማኙ አገልግሎት በጣም አስፈላጊ የሆነ እውነት ሲገልጥ፤- "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፣ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ" በማለት ተናገረ። አማኙ ለመንፈሳዊ እድገቱ ወይም ብስለቱ ማስረጃ የሚሰጠው ኢየሱስ ያደረገውን ሥራ እርሱ ደግሞ በመስራት ነው። የኢየሱስ የራሱ ሥራ እንዳከበረው እነዚህ ሥራዎች እግዚአብሔር አብን ያከብራሉ።

(5). የኢየሱስ አገልግሎት በምድር ላይ የሚከናወነው እንዴት ነው?

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የመንፈሳዊ እድገትን ወይም ብስለትን ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳንድ ጊዜ የሚያገናዝበው ከእርሻ ጋር ነው። ስለ አማኙ አገልግሎት ለማስተማር ኢየሱስ የተጠቀመው በዚህ ምሳሌ

ነው። በዮሐ 15:16 ላይ ስለዚሁ ሲገልጽ፦ "እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፣ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ" በማለት ይናገራል። በዚሁ ላይ ኢየሱስ ጠቃሚና አስፈላጊ ትምህርት መስጠቱን በመቀጠል እርሱ እውነተኛ የወይን ግንድ እንደሆነ ገበሬውም አባቱ እንደሆነ ከተናገረ በኋላ አማኞች ቅርንጫፎች መሆናቸውን በመግለጽ ከግንዱ ጋር አስካሉ ድረስ ፍሬ የሚያፈሩ መሆናቸውን አስረድቶአል።

(6). በዮሐ 15:7 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት አማኙ በፀሎት የሚጠይቀውን ከኢየሱስ ለማግኘት አማኙ መፈጸም ያለበት ሁኔታ ምንድነው?

(7). በዮሐ 15:10 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት በኢየሱስ ፍቅር ውስጥ ለመኖር አማኙ ምን ማድረግ አለበት?

የአማኙ ፍሬያማ መሆን የአገልግሎቱ ማስረጃ ነው። እያንዳንዱ አማኝ ግን ማስታወስ ያለበት በአገልግሎቱ የኢየሱስን አገልግሎት እየፈፀመ እንደሆነ ነው። በዮሐ 15:5 ላይ እንደተጻፈው አማኙ ያለ ክርስቶስ "ምንም ማድረግ አይችልም።"

መንፈሳዊ ብስለትን በሥራ መግለጽ

ዓላማ 4 በሐዋ 6:1-7 ላይ የተመረጡት ሰባት ሰዎች መንፈሳዊ እድገታቸውን ወይም ብስለታቸውን በማስረጃ እንዴት እንዳሳዩ ለመግለጽ።

ጠቃሚ ሆኖ እስመገኘት ያለ ማደግ ወይም ያለ መብሰል ምልክት እንደሆነና ምን ያህል አሳዛኝ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። በዕብ 5:12 ላይ ስለዚሁ ሲገልጽ፦ "ከጊዜው የተነሣ አስተማሪ ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነት ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኋልና" ይላል። ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚፈልገው የመንፈሳዊ እድገትን ወይም ብስለትን ማስረጃ ነው። እያደጉ የሚሄዱ ክርስቲያኖች ጠቃሚ አገልግሎትንም ያበረክታሉ። ጳውሎስ እዚህ ላይ ለማስረጃ ይፈልገው የነበረው የማስተማር አገልግሎትን ነበር። በ2ጢሞ 3:16-17 ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለዚሁ አስፈላጊ ጉዳይ ሲናገር፦ "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"

"ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ" የሚለው ሐረግ መንፈሳዊ እድገትን ወይም ብስለትን የሚገልጽ ሐረግ ነው። ብስለት ወይም እድገት ማለት "ወደ ምልዐት ለመምጣት መሰናዳትና መዘጋጀት" ማለት ነው። የእግዚአብሔር ዓላማ እኛን ወደ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት በቃሉ

በኩል ወደ ምልዐት ለማምጣት ነው። ዘዚያን ጊዜ ነው እርሱን የሚያከብር ሥራ መሥራት የምንችለው፣ የሚከተለው መልካም ሥራ እኛ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀን ለመሆናችንና በኢየሱስ ክርስቶስ እያደግንና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እየበሰልን ለመሄዳችን ማስረጃ ነው።

(8). የሐዋ 6፡1-7 በጥንቃቄ ካነበብክ በኋላ በቤተ ክርስቲያን አንድ ታላቅ ችግር ተፈጥሮ እንደነበረና ችግሩን ለመፍታት ሐዋርያት በአገልግሎት የበሰሉ ሰባት ሰዎች እንዲመርጡ ምዕመናንን እንዳዘዙ ትረዳለህ። በቁ. 3 ላይ የሚመረጡት ሰዎች ማሟላት ያለባቸውና ለብስለታቸው ማስረጃ የሆኑ ሁለት ነገሮች ተጠቅሰዋል። እነዚህን ሁለት ነገሮች በባዶው ስፍራ ጻፍ። እነዚህ ሰባት ሰዎች_____ና_____የተሞሉ መሆን አለባቸው።

(9). እነዚህ ሰባት የበሰሉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ለማስገኘት አስፈላጊ በሆነው ስፍራ ተመደቡ (ሐዋ. 8፡1-7)። እነዚህ ሰባት ሰዎች የመንፈሳዊ ሕይወታቸውን እድገት ወይም ብስለት ማረጋገጫ ያሳዩት እንዴት ነበር?

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስያስ ለነበሩ ስለ ቀድሞ ክርስቲያኖች የጸለየው ጸሎት በቆላ 1፡9-10 ላይ ሲናገር፦

> ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም፣ በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ . . . ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን ይላል።

(10). በቆላ 1፡10 ላይ በተጻፈው መሠረት የአማኙ ሕይወት ጌታን በሚያስደስት ስፍራ ላይ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድነው? ጥቅሱን በጥንቃቄ በማንበብ ትክክለኛ መልሱን ስጥ።

ሀ. አማኙ በአጠቃላይ እያደገ መሆኑ።
ለ. አማኙ ኃጢአት ከመሥራት በመቆጠቡ።
ሐ. የአማኙ ሕይወት መልካም ሥራዎችን በማፍራቱ።
መ. አማኙ ዘወትር ከሌሎች ጋር ሕብረት በማድረጉ።

በኤፌ 2፡8-10 ላይ የተጻፈው ቃል እግዚአብሔር እኛን ለምንና እንዴት እንዳዳነን አጣምሮ የሚገልጽ ነው። የአማኙ መልካም ሥራዎች አስፈላጊነት ላይ ስናተኩር ሳለን፣ ሰው መዳን የሚችለው በጸጋ ብቻ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

(11). በኤፌሶን 2፡8 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ሰው መዳን የሚችለው እንዴት ነው?

ይህንን ክፍል ከመደምደማችን በፊት ስለ አማኙ ሥራዎች የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ደግመን ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው።

❶. ሰው ይቅርታ ያገኘው ወይም የዳነው በሥራው አይደለም። ሰው የሚድነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በከፈለው መስዋዕት በኩል በእምነት ብቻ ነው። የሰውን የኃጢአት ዋጋ የከፈለው የክርስቶስ ሞት ነው። እዚህ ሰው ሊድን የሚችለው በእግዚአብሔር ጸጋ ሲሆን፣ ይህም ጸጋ እግዚአብሔር ለእኛ ለማይገባን ሰዎች ያለውን ነፃ ፍቅርና ምህረት የሚያሳይ ነው።

❷. መልካም ሥራዎች ጎጢአተኛውን ወይም አማኙን ሊያድኑ ባይችሉም፣ የክርስትና ሕይወት ዓላማና ግብ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። ጠቃሚ የሆነ ሕይወት በመኖር እግዚአብሔርን ለማክበር በዓላማ የተፈጠርን መሆናችንን ዘወትር ልናስታውስ ይገባናል።

በመንፈስ ቅዱስ መቀጠል

ዓላማ 5 መንፈስ ቅዱስ በባሕርይና በሥራ እንዴት ከክርስቶስ ጋር ሊያገናኘን እንደሚፈልግ ለመግለጽ።

መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ ሕይወት ይሰጠዋል ስለዚህ አማኙ መንፈስ ቅዱስ ሕይወቱን እንዲቆጣጠር ማድረግን መማር አለበት። እስካሁኑ ያተኮርነው በዚሁ ጥናት ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስ ባሕርያችንን መቆጣጠሩን የምናረጋግጥበት የክርስቶስ ባሕርይ በእኛ ዘንድ መገኘት ነው። መንፈስ ቅዱስ አእምሮአችንንና ፈቃዳችንን መቆጣጠሩን የምናረጋግጥበት ግን በሥራችን ነው። እነዚህም ሥራዎች የክርስቶስን አገልግሎት መቀጠልና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆኑ መልካም ተግባራት ናቸው።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያደርግ ዘንድ ለአማኙ የሚሰጡ ልዩ ችሎታዎች ናቸው። በሮሜ 12 ላይና በ1ቆሮ 12 ላይ ስለነዚህ ልዩ ችሎታዎች የሚያስተምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። በሮሜ 12፡5-6 ላይ ስለዚሁ ሲናገር፦ "እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፣ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችንም የሌላው ብልቶች ነን፥ እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን" ይላል።

የአማኞችን ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በምሳሌነት የሚያስረዱን የአካላችን ብልቶች አባላት ልዩ ልዩ ተግባሮች ናቸው። ጣቶቻችን የተለዩ ተግባራት ማከናወን አለባቸው። አንዳንድ ነገሮችን፥ ዕቃዎችን መያዝ መቻል አለባቸው። አንድ ነገር በወረቀት ላይ ለመጻፍ በንፈልግ የእጅ ጣቶቻችን እርሳሱን በሚገባ በመያዝ መቆጣጠር አለባቸው። የእግር ጣቶች ግን እንደ እጅ ጣቶች ለመሆን አይችሉም። የእግር ጣቶቻቸውን እንደ እጅ ጣቶቻቸው ሊጠቀሙ የሚችሉ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው። ቢሆንም

የእግር ጣቶቻችን ሚዛናችንን ጠብቀን ለመራመድ እንደዚሁም ለመሮጥ ያገለግሉናል።

(12). በሮሜ 12:6-6 ላይ ሰባት የአማኝ አገልግሎቶች ተዘርዝረው ታገኛለህ። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ለምሳሌነት ተጠቅሰዋል። የቀሩትን አምስቱን በክፍቱ ቦታ ሙላ።

ሀ. የእግዚአብሔርን መልእክት መናገር
ለ. ማገልገል
ሐ. _____
መ. _____
ሠ. _____
ረ. _____
ሰ. _____

1ቆሮ 12፡ 4-7፡- ከመንፈስ ቅዱስ ስለሚገኙ ስጦታዎች በግልጽ የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ስለ ስጦታዎች ሲናገር፡-

"የአጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፣ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፣ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል" ይላል።

(13). በ1ቆሮ 12:8-11 ላይ ደግሞ በመቀጠል የተዘረዘሩት ዘጠኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ናቸው። ከነዚህ ስጦታዎች ሦስቱ ከመናገር ጋር የተያያዙ ናቸው። እነዚህን ከሌሎቹ ለይተህ በተሰጠው ስፍራ አሰፍራቸው።

ሀ. ___ _____ ለ. _____ ሐ. _____

በዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ሌሎቹ ሦስት ስጦታዎች ከልዩ መንፈሳዊ ኃይል ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፣ እነርሱም (1) ልዩ የሆነ የእምነት ኃይል፣ (2) የፈውስ ኃይልና (3) ተአምራትን የማድረግ ኃይል ናቸው። እነዚህ ልዩ ኃይሎች ኢየሱስ ያደረጋቸውን አስገራሚ ሥራዎች አማኙም እንዲሠራ ያስችሉታል።

በ1ቆሮ 12:8-11 ላይ የተዘረዘሩት የመጨረሻ ሦስቱ ስጦታዎች ከሰው ደረጃ በላይ ለማሰብና ለማስተዋል እንዲቻል የሚያደርጉ ናቸው። እነርሱም፡- (1) የጥበብ ቃል፣ (2) የእውቀት ቃል፣ (3) ከመንፈስ ቅዱስ የሆኑትን ስጦታዎችና ያልሆኑትን ለይቶ የመናገር ስጦታዎች ናቸው።

እነዚህ ልዩ ስጦታዎች የኢየሱስን አምሳልነት የሚያሳዩ ልዩ ሥራዎችን፥ እግኙ ለማከናወን እንዲችል ያደርጉታል። እነዚህ ስጦታዎች የሰዎችን ፃሳብ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሳብ እንጂ ስጦታው ወደ አለው ሰው ለመሳብ መሆን የለበትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህ ስጦታዎች እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንዳለባቸው የሚነግረን በ1ቆሮ ምዕራፍ 14

ላይ የተጻፈው ነው። ለእኛም ጥሩ ማስታወሻ ሊሆነን የሚገባን በ1ቆሮ 14:12 ላይ የተጻፈው ቃል ሲናገር፡- "እንዲሁም ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ" ይላል።

(14). አማኞች እንደመሆናችን መጠን ባሕሪያችንንና ተግባራችንን እንደ ፍላጎቱ ለመለወጥ እንዲችልና ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠረን ሕይወታችንን ለመንፈስ ቅዱስ ማስረከብ አለብን። መንፈስ ቅዱስ በባሕርይና በሥራችን ከክርስቶስ ጋር ሊያገናኘን የሚፈልገው እንዴት ነው?

ማጠቃለያ

በማቴ 21:26-31 ላይ ኢየሱስ ስለ ሁለት ልጆች ታሪክ የተናገረው ቃል ሰፍሮ እናገኛለን። አባትየው ወደ ታላቁ ልጅ ቀርቦ፡- "ልጄ ሆይ፣ ዛሬ ሂድና በወይኔ አትክልት ሥራ" አለው። እርሱም መልሶ፡- "አልወድም" አለ። ኋላ ግን ተጸጸተና ሄደ። ወደ ሁለተኛውም ቀርቦ እንዲሁ አለው። እርሱም መልሶ፡- "እሺ ጌታዬ" አለ፣ ነገር ግን አልሄደም። ከዚያም ኢየሱስ የሚያደምጡትን ከነዚህ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ ያደረገው የትኛው እንደሆነ ጠየቀ። የሚያደምጡትም ሰዎች ፊተኛው አሉት። ኢየሱስ በተናገረው ታሪክ ውስጥ መልዕክቱ ግልጽ ነው። መልዕክቱ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ማውራት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው። ለመንፈሳዊ ብስለት ዋናው ማስረጃ ጠቀሜታ ያለው ሕይወት ነው።

(15). በማቴ 25:34-36 ላይ ጻድቃን ሰዎች ስላከናወኑት ስድስት መልካም ተግባራት ይጠቅሳል። የመጀመሪያውን ምሳሌ እንዲሆን ስለጠቀስነው የቀሩትን አምስቱን ጥቀስ።

ሀ. የተራቡትን ማብላት
ለ. _____
ሐ. _____
መ. _____
ሠ. _____
ረ. _____

በማቴ 25:37-40 ላይ እንደተገለጸው ለተቸገሩ ሰዎች ያደረጉት መልካም ሥራዎች ለእርሱ እንዳደረጉለት እንደሚቆጠር ለዓድቃን እንደነገራቸው ማስተዋል አስፈላጊ ነው። በማቴ 5:16 ላይም፣ "መልካም ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" በማለት ተናግሮአል። ሌላም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለዚሁ ማጥናት እንችላለን። ሆኖም እንድንረዳ የሚያስፈልገው የእኛ ዓላማ በመንፈሳዊ ሕይወታችን መብሰላችን ዋናው ማስረጃ ጠቀሜታ ያለው የክርስትና ሕይወት መኖራችን ነው።

የመከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት። እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" የሚለውን ፊደል በባዶው ቦታ ላይ ሙላ።

___1. ሰው በዓሣ፣ በአእዋፍ በእንሰሳት ላይ ሥልጣን እንዲኖረው እግዚአብሔር አደረገ።
___2. ኢየሱስ ካደረገው ተግባራት ይልቅ መጥምቁ ዮሐንስ ስለ እርሱ የመሰከረለት ይበልጣል።
___3. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአማኙ ሕይወት እንደ ኢየሱስ መልካም ተግባራትን ለማከናወን ያስችሉታል።

እጭር መልስ። በተሰጠው ክፍት ቦታ ትክክለኛውን መልስ ጻፍ

4. "ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ" የሚለው ሐረግ ምንን የሚገልጽ ነው? _____

በ1ቆሮ 12:8-11 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት በመናገር በኩል ለክርስቲያኖች መለኮታዊ ችሎታ የሚሰጡት ሦስቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ምንድን ናቸው?

5. _____ 6. _____ 7. _____

በማቴ 25:34-36 ላይ ጻድቃን ሰዎች ከሚፈጽሟቸው ከስድስቱ መልካም ተግባራት ውስጥ ሦስቱን ዘርዝር።

8. _____ 9. _____ 10. _____

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሐ

9. ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ሥራ በመሥራት

2. ሀ. ቀን ሳለ ለ. በጨለማው ጊዜ

10. ሐ

3. በአባቱ ሥልጣን ያደረጋቸውን ነገሮች

11. በእምነት በእግዚአብሔር ጸጋ

4. አባቱ ሥራውን ስለሰጠው

12. ሀ. ምሳሌውን ተመልከት
ለ. ምሳሌውን ተመልከት
ሐ. ማስተማር
መ. ሌሎችን ማበረታት
ሠ. ከሌሎች ጋር መካፈል
ረ. ሥልጣንን መጠቀም
ሰ. ቸርነትን ማሳየት

5. በአማኞች በኩል

13. ሀ. የእግዚአብሔርን መልእክት መናገር
ለ. በአዲስ ልሳን መናገር
ሐ. በአዲስ ልሳን የተነገረውን መተርጎም

6. እርሱ በኢየሱስ ውስጥ፥ ቃሉም በእርሱ ውስጥ መኖር አለበት።

14. የእግዚአብሔር መንፈስ የክርስቶስን ባሕርይ በእኛ ውስጥ በመመሥረት የእርሱን ሥራዎች በእኛ ውስጥ ለማሳየት ይፈልጋል።

7. የኢየሱስን ትዕዛዛት መፈጸም

15. ሀ. (ምሳሌውን ተመልከት)
ለ. ለተጠማ ማጠጣት
ሐ. እንግዳ መቀበል
መ. የታረዘ ማልበስ
ሠ. የታመመ መጠየቅ
ረ. የታሰረ መጠየቅ

8. መንፈስ ቅዱስን፣ ጥበብን

10 የመንፈሳዊ ለውጥ ማስረጃ

ትምህርት

ወደ መጨረሻው ክፍለ ትምህርት በመድረሳችን ደስ ሊለን ይገባል። አንድ አስፈላጊ የሆነ ነገር እከናውነን ስንጨርስ ዘወትር የደስታ ስሜት ይሰማናል። ይህንንም የመጽሐፍ ቅዱስ ተከታታይ ትምህርት በማገባደዳችን ደስታ ሊሰማን ይገባል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በሚገባ እንድንተዋወቅና ለእግዚአብሔር ሃሳብ ቅርብ ወደ ሆነው ወደ መንፈሳዊ እድገት የሚመራን ነው።

በክርስትና ሕይወት አያደጉ ወይም እየበሰሉ መሄድ ማለት ምን እንደሆነ እስከአሁን ድረስ ስንከታተል ከቆየን በኋላ፥ የክርስቲያን እድገት ወይም መብሰል ማስረጃ ምን እንደሆነ በመጨረሻ ተመልክተናል። ከትምህርት 8 እስከ ትምህርት 10 የተሰጡትም ተከታታይ ትምህርቶች የራሳችንን መንፈሳዊ እድገት ለመለካት የሚረዱን መለኪያዎች ይሰጡናል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አያደጉ የሚሄዱ ክርስቲያኖች ነገሮችን እንደ ኢየሱስ ማየትና ማድረግ ይጀምራሉ። በሕይወታቸውም የእርሱን ባሕርይና ተግባራት መያዝና ማከናወን ይፈልጋሉ።

ይህን ዓላማና ግብ ስትመለከት በጣም አስቸጋሪ ስለሚመስል ምናልባት ትንሽ ተስፋ ትቆርጥ ይሆናል። ሰዎች በመሆናችን፥ በዚህ ምድር ላይ ኢየሱስ ካከናወናቸው ነገሮች ጋር ራሳችንን ማወዳደር አስቸጋሪ መስሎ የሚታይ ነገር ቢሆንም እግዚአብሔር ያሰፈረው መመዘኛውን ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ግብ ለመድረስ እንድንችልም ሊረዳን ዝግጁ ነው። ደካሞች ሰዎችን ወስዶ በእነርሱ በኩል ታላቅ የመለወጥ ኃይሉን ማሳየት የእግዚአብሔር ትልቅ ደስታ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠራንበት ታላቁ ተስፋችን ይህ ነው።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- በድካም ውስጥ ብርታት
- ጥርጥርና በራስ ላይ መፍረድ
- በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሚገኝ ለውጥ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በለው ድካም የእግዚአብሔር ክብር እንዴት እንደሚታይ ለማስረዳት

- በሰዎች ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን የመለወጥ ኃይል ውጤት ለመግለጽ፥ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ለማቅረብ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. እሥረኛውን ትምህርት በጥንቃቄ አንብብ።
2. በትምህርቱ ዝርዝር ላይ የተሰጡትን ጥያቄዎች ካጠናቀቅህ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ።
3. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና ከመስድክ በኋላ መልሶችህን ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

በድካም ውስጥ ብርታት

ዓላማ 1 የአማኙን የኃይል ምንጭና ድካም ለይቶ ለማስረዳት።

ስለ አዕዋፍ የሚያጠኑ ሰዎች እንደሚነግሩን ወፎች ርቀት ወዳለው ስፍራ ሲሄዱ የሚበሩት በከፍታ ነው። በከፍታ የሚበሩበትም ሦስት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው በከፍታ የሚበሩበት ምክንያት በሚበሩበት ጊዜ በተሻለ መንገድ ሁሉን ለማየት እንዲችሉና አቅጣጫቸውን በቀላሉ ለማግኘት እንዲችሉ ነው። በሁለተኛ ደረጃ አነርሱን ከሚያድኑአቸው ሌሎች አእዋፍ በላይ በመሆናቸው ስጋት የለባቸውም። ሦስተኛ፥ በከፍታ በሚበሩበት ጊዜ አየሩ ቀለል ያለ ስለሆነ በፍጥነት እንዲበሩ ይረዳቸዋል። እነዚህ ምክንያቶች ሁሉ ርቀት ያለውን ዓላማቸውን እግቡ ለማድረስ እንዲችሉ ያደርጉአቸዋል።

አማኙ ከዚህ የሚማረው ነገር ቢኖር በጥርጥር በተሞላ ጊዜ ሕይወቱን የሚመለከተው በዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ መንገዱን ለማየት ያዳግተዋል፥ ዲያብሎስም ይፈትነዋል። እግዚአብሔር ወደ ሚመለከተው ወደ ንጹሁ የሕይወት አየር ከፍ ሲል ብቻ ነው ወደ እግዚአብሔር ዓላማ ለመድረስ አስፈላጊውን መንፈሳዊ ብርሃንና ኃይል የሚቀበለው።

ምናልባት፦ "እኔ ወደ መንፈሳዊ እድገት ወይም ብስለት ለመድረስ አልችልም! ደካማ ነኝ!" ብለህ ታስብ ይሆናል። እንዴት እንደ ኢየሱስ መሆን እችላለሁ? የሚል ጥርጣሬ ቢሰማህም ያ ዝንባሌ ራሱ የትክክለኛው አቅጣጫ መንደርደሪያ ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው በራሱ ችሎታዎች ብርቱ እንደሆነ ሲሰማው በራሱ ላይ ወደ መደገፍ ያዘነብላል። የራሱን ድክመት ሰይቶ የሚያውቅ አማኝ ችግሩን በተሻለ መንገድ በመገንዘብ ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር ሊመለከት ይችላል።

(1). የእማኙ የብርታትና የድካም ምንጭ ምን እንደሆነ ግለጽ።

የእግዚአብሔር ክብር

ዓላማ 2 በ1ቆሮ 1፡26-31 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት አማኙ የሚመካበት ነገር ምን እንደሆነ ለመግለጽ።

ያለ እግዚአብሔር የሆነ ሰው በአመጽና በኃጢአት ነፃነቱን ለማሳየት እንደሚሞክር ተመልክተናል። የሰውን ጥበብ ከፍ በማድረግ በሰው ኃይል ይመካል። የየዘመኑ የሰልጣኔ ታሪክ የሚነግረን ይህንኑ ነው። ከእርሱ ጋር በትክክል ለመቆም እግዚአብሔር የመረጠው ከዓለም አስተሳሰብ ጋር አብሮ የማይሄደውን የክርስቶስን መሥዋዕትነትና እምነትን ነው።

በ1ቆሮ 1፡21 ላይ ጳውሎስ የወንጌልን መልዕክት "እንደ ሞኝነት መልዕክት" እድርጎ ያቀርበዋል። በእግዚአብሔር ላይ መደገፉን የሚጠይቅ መልዕክት ነው። ይህን መልዕክት ዓለም አይቀበለውም። ስለዚህም መልዕክት እውነተኛነት ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 1፡26-31 ላይ ሲገልጽ፦

> "ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁን ተመልከቱ፤ እንደሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፥ ኃያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ። ነገር ግን፦ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው"

በማለት ይናገራል።

(2). በ1ቆሮ 1፡26-31 ላይ እንደተገለጸው የአማኙ ጥበብ

ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
ሐ. የአእምሮው እድገቱ ነው።

(3). በዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደተገለጸው አማኙ መመካት ያለበት በምንድን ነው?

እግዚአብሔር የሚጠቀምበትን መሣሪያ ሳይሆን እግዚአብሔርን ራሱን ሰው እንዲያከብረው ይፈልጋል። የሚጠቀምበት መሣሪያ ብርቱና የሚያምር ሲሆን ማድረግ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል። በራሳችን ምንም ማድረግ እንደማንችል ስለምናውቅ ይህ ብዙዎቻችንን ሲያበረታታን

ይጠብቃል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ክብሩን በእኛ ውስጥ ለመግለጽ ትልቅ እድል ያገኛል።

በደካማ ሰው ውስጥ ክብሩን የመግለጹ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት ነው። ጳውሎስ በጣም የተማረ ሰው ቢሆንም፣ ድካሞች ነበሩበት። ከነበሩበት ድካሞች አንዱ በ2ቆሮ 12፡7-8 ላይ፦ "በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎሰመኝ የሰይጣን መልዕክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው። ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁት" በማለት የሚናገረው ነው። እግዚአብሔርም በ2ቆሮ 12፡9 ላይ ለዚህ ጥያቄው የሰጠው መልስ፦ "ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካምህ ይፈጸማልና" በማለት ነበር።

ከዚያም ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ 12፡9-10 ላይ፦ "እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ። ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም፣ በችግርም፣ በደስታም፣ በጭንቀትም፣ ደስ ይለኛል፤ ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና" በማለት ለመጻፍ እንደቻለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት እንችላለን። እግዚአብሔር እንድናከብረው ስለሚፈልግ፣ በምናደርገውና በምንናገረው ሁሉ እርሱን ለማክበር እንሞክር።

የእግዚአብሔር ኃይል

ዓላማ 3 ሕዝ 2፡2 ላይ ያለውን ቃል መሠረት በማድረግ ሕዝቅኤል በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ምን እንዳስቻለው ለመግለጽ።

በሰው ደካማነት ውስጥ እግዚአብሔር ክብሩን የገለጠበት ሌላው ምሳሌ የብሉይ ኪዳኑ ነቢይ የነበረው ሕዝቅኤል ነው። ሕዝቅኤል እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ የሰላሳ ዓመት ካህን ነበር። በዚያን ጊዜ አገሩና ሕዝቡ በጠላቶቻቸው ድል ሆነው የተደመሰሱበት ወቅት ነበር። የእርሱም የሕይወት ዓላማ (ካህን መሆኑ) ጥቅም የሌለው ከንቱ ነገር ሆኖ ነበር። ነቢዩም በዚያን ወቅት ምርኮኛ ሆኖ በእርሻ ላይ ተሰማርቶ ያገለግል ነበር። በዚህ ሁኔቴ ላይ ሳለ በሕዝ. 1 እና 2 ላይ እንደተጻፈው የእግዚአብሔር ጥሪ ወደ እርሱ መጣ። ጥሪው የመጣው በዚህ ኃይለኛ ማዕበል ውስጥ ነበር (ሕዝ 1፡4)። ይህ ጥቅስ ሕዝቅኤል በሕይወቱ የገጠመውን መደነጋገር ሳያመለክት አልቀረም። እግዚአብሔር በዚህ ማዕበል ውስጥ ኃይሉን ገለጠ። ሕዝ. 2፡1-3 ላይ ሕዝቅኤል ስለዚሁ ሲያብራራ፦

> ይህን በተመለከትኩ ጊዜ በግንባሬ በምድር ላይ ተደፍቼ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ፦ እርሱም፣ የሰው ልጅ ሆይ፣ በእግርህ ቁም እኔም እናገርሃለሁ አለኝ። በተናገረኝም ጊዜ መንፈስ ገብቶኝ በእግሬም አቆመኝ፥ የሚናገረኝንም ሰማሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ። የሰው ልጅ ሆይ፥ በእኔ ላይ ወደ ዐመፁ ወደ አመጸኞች ሰዎች ወደ እስራኤል ልጆች እልክሃለሁ አለኝ።

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን በጠራበት ወቅት "ሟች ሰው" ወይም "የሰው ልጅ ሆይ" በማለት የተጠቀመበት ቃል ሕዝቅኤል ሰው መሆኑን እንዲገነዘብ የሚያደርግ ኃይለኛ ቃል ነው። እግዚአብሔር በሰው በኩል ለመሥራት እንደሚፈልግ ሕዝቅኤልን የሚያሳስብ ነው። *ሕዝቅኤል* የሚለው ስም ትርጓሜው፦ "እግዚአብሔር የሚያበረታው ሰው፣" ወይም "የግሉ ጠባይ ራሱ እግዚአብሔር የሚያበረታታ ለመሆኑ ማስረጃ" የሆነ ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ሰው በአሁኑ አነጋገር፦ "ያ ሰው ማንኛውንም መልካም ነገር ቢሠራ እግዚአብሔር በእርሱ አድሮ ያደረገው እንደሆነ ሰዎች ይረዳሉ!" ሕዝቅኤል እንደዚህ የምንለው ዓይነት ሰው በመሆኑ በስሙም ሆነ በድርጊቶቹ ለእኛ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ነው።

(4). በሕዝ 2:2 ላይ የተጸፈውን ቃል ካነበብክ በኋላ የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ፡ ሕዝቅኤል በእግዚአብሔር ራት እንዴት ሊቆም ቻለ?

ሀ. በራሱ ኃይል ተነሥቶ
ለ. የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስላስነሣው
ሐ. የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ገብቶ ስላስነሣው

የሕዝቅኤል ባሕርይ የተለወጠው በእግዚአብሔር ኃይል ነበር። በእግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል ብቻ ደነግማ የነበረውና ግራ የተጋባው ሕዝቅኤል ጸንቶ መቆም መቻሉን በሕዝ 12:7 ላይ ሲገልጽ፦ "እንዳዘዘኝም አደረግሁ" ይላል። ከረጅምና ከፍሬያማ አገልግሎቱ፡ እግዚአብሔር ነብሩን ተቀበለ።

ሞርሞርኖ በራስ ላይ መፍረድ

እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ የተጠሩ ብዙ ሰዎች ሥራውን በራሳቸው ስማከናወን እንደማይችሉ ተሰምቶአቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት በራሱ ስህተት አይደለም። ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በሰራን በእግዚአብሔር ላይ እምነት የማጣትን ስሜት የሚያመለክት ነው። ይህ ዓይነቱ፡ ሁኔታ ደነግማ የሆነ ክርስቲያን በራሱ ላይ እንዲፈርድና የህሊና ዐዐት እንዲያድርበት ሊያደርገው ይችላል። እግዚአብሔር ድነግማችንን በሙሉ ያውቃል። ሰጠራን አገልግሎትና ሥራ ብርታትና ኃይል የሚሰጠን እርሱ ራሱ ነው። መጠራጠርና በራሳችን ላይ መፍረድ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ዓላማ እንዳንፈጽም እንዲያደርገን ከጋበገን በእርሱ ላይ እምነት ማጣታችንን የሚያመለክት ነው።

ችሎታችንን መጠራጠር

ዓላማ 4 መንፈሳዊ እድገቱ በሁሉ ነገር ይታይ ዘንድ ጢሞቴዎስ እንዲ ለማመድ የተነገረውን አራት ነገሮችን ለመሣለጽ።

በዘጸ ምዕራፍ 3 ላይ እንዲያገለግለው እግዚአብሔር ሙሴን እንደጠራው ይነግረናል። ሙሴም እግዚአብሔርን ማገልገል መቻሉን በመጠራጠሩ፣ እግዚአብሔር በተአምራዊ መንገድ ከሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ በተናገረው ጊዜ በቁ. 4 ላይ "እነሆኝ አዚህ ነኝ" ሲል መለሰ። ሕዝቡንም በመምራት ከግብፅ ምድር ያወጣ ዘንድ ወደ ግብፅ ንጉሥ እንደሚልከው እግዚአብሔር ነገረው። ሙሴም ወዲያው በቁ. 11 ላይ፦ "እኔ ምንም አይደለሁም፣ እንዴት አድርጌ ነው? እኔ ወደ ንጉሡ ሄጀ የእስራኤልን ሕዝብ ማውጣት የምችለው?" ሲል መለሰ። እግዚአብሔርም በቁ. 12 ላይ፦ "እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ እኔም እንደላክሁህ ምልክትህ ይህ ነው፣ ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር ትገዛላችሁ" አለው።

ከዚያም ሙሴ በተከታታይ ምክንያቶቹን መዘርዘር ጀመረ። በቁ. 13 ላይ፦ "ማነው ቢሉኝ ምን እላቸዋለሁ?" የሚል ምክንያት ሲያቀርብ በ4:1 ላይ ደግሞ "አያምኑኝም፣ እግዚአብሔር አልተገለጠልህም ቢሉኝስ?" የሚል ምክንያት አቀረበ። ከዚያም በቁ. 10 ላይ የመጨረሻ ምክንያቱን ሲሰጥ፦ "እኔ መናገር የማልችል ሰው በመሆኔ እኔን አትላክ" በማለት ሲናገር፣ እግዚአብሔርም "የሰውን አፍ የፈጠረ ማነው? ዲዳነ፣ ደንቆሮነ፣ የሚያይነ፣ ዕውርነ የሚያድርግ ማነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን?" በማለት በቁ. 11-12 ላይ "እንግዲህ አሁን ሂድ፣ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፣ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ" አለው። አሁንም ሙሴ አይሆንም፣ "ጌታ ሆይ፣ በምትልክበት ሰው እጅ ላክ" በማለት በቁ. 13 እንደተናገረ አዚህ ነጥብ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ።

በዚህ በሙሴ የጥሪ ታሪክ ውስጥ የምናየው የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ልብ አድርገን እንድንመለከት የሚረዳን ነው። እግዚአብሔር የሙሴን ችግርና ጥርጣሬ ሁሉ ስላወቀ ሙሴ ለሚያቀርበው ምክንያት ሁሉ በትዕግሥት መልስ በመስጠት ከእርሱም ጋር አብሮ እንደሚሠራ ነገረው። ነገር ግን ጉዳዩ እምነት የማጣት ጉዳይ የሆነበት ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ክርክሩን ቀጠለ። በመጨረሻም ሙሴ በመታዘዝ ወደ ግብፅ ሄደ። እግዚአብሔርም በየዕለቱ እየረዳው ሲሄድ እምነቱ እያደገ ሄደ። የእግዚአብሔርም ሕዝብ ታሳቅ መሪ ለመሆን በቃ።

የመንፈሳዊ እድገት ዓላማና ግብ አስቸጋሪ ቢመስልም እማኞች እንደ መሆናችን መጠን ዋናው ፍላጎታችን በሕይወታችን ታላቁን የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመፈጸም መሆን አለበት። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን ስንሄድ የበለጠ ሥራና ሃላፊነት እንደሚጠብቀን ስንረዳ እንደ ሙሴ ችሎታችንን መጠራጠር ደረጃ ላይ እንደርስ ይሆናል። እግዚአብሔር ሲጠራን ግን እንደሚረዳን የሰጠንን ተስፋዎች መዘንጋት የለብንም። ሁለንተናችንን የሰራው እግዚአብሔር በመሆኑ እኛ ራሳችንን ከምናውቀው በላይ እርሱ አብልጦ ያውቀናል። *የራሳችንን አቅመ ቢስነት በእግዚአብሔር ላይ በምናደርገው የእምነት ልምምድ ልንቋቋመው ይገባል።* እርሱ የኃይልና የሥልጣን አምላክ በመሆኑ የእርሱ ክብር የሚታየው ታላላቅ ነገሮችን ለማድረግ በደካማ ሰዎች ሲጠቀም ነው።

(5). በ1ጢሞ 4:11-16 ላይ የተጻፈውን አንብብ። በቁ. 12 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ጢሞቴዎስ ታናሽነቱን ማንም እንዳይንቀው የተመከረው

ሀ. መልከ መልካም ባለመሆኑ ነው።
ለ. ወጣት በመሆኑ ነው።
ሐ. ደካማ በመሆኑ ምክንያት ነበር።

(6). በ1ጢሞ 4:13-15 ላይ እድገቱ በሁሉ ዘንድ ሊታይ ይችል ዘንድ እንዲለማመድ የተነገረውን አራት ነገሮች በቅደም ተከተላቸው መሠረት አስፍራቸው።

ሀ. _____ ሐ. _____
ለ. _____ መ. _____

በሰይጣን ክስ ምክንያት የሚመጣ ጥርጣሬ

ዓላማ 5 የጥርጥርን ዋና ምንጭ ለይቶ ለማወቅና እንዴት ለመቋቋምና ለማስወገድ እንደሚቻል ለመግለጽ።

ብዙ ጊዜ ሰይጣን ራሳችንን እንድንጠራጠር ያደርገናል። ቀደም ሲል እንደተመልከትነው እርሱ የአማኞች ተቃዋሚ ነው። እርሱ አማኞችን ግራ ወደ ማጋባት ለማምጣት አጥብቆ ይጥራል። በአማኞች ላይ ደካማ ጎናቸውን በመጠቆም ክስ ያመጣል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ሰይጣን በሚያመጣባቸው ክስ ምክንያት የእርሱን ውሸት በመቀበልና በማመን ተስፋ ይቆርጣሉ። እርሱ የሚነግራቸውን ነገር፥ ስለ ራሳቸው ካላቸው ስሜት ጋር በማገናኘት እውነት መሆኑን በማረጋገጥ ራሳቸውን ይኮንናሉ።

እግዚአብሔር ከ70 ዓመታት ምርኮ በኋላ፥ ሕዝቡ ወደ አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ባደረጋቸው ጊዜ የተመረጠው መንፈሳዊ መሪ ኢያሱ ነበር። ሊቀ ካህኑ እርሱ ነበር፣ (ይህ በመጀመሪያ ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራው ኢያሱ ሳይሆን፥ ሌላ ኢያሱ ነው)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሱ ወዲያውኑ ቤተ መቅደሱን መልሰው ማነጽ ቢጀምሩም ብዙ ሳይቆዩ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ገጠማቸው። የገጠማቸውም ተቃውሞና ማጉረምረም ነበር። የቤተ መቅደሱ መሠረት ከተጣለ በኋላ ተስፋ በመቁረጥ ምክንያት ሕዝቡ ለ16 ዓመታት ሥራውን አቋረጡ። በመጨረሻም እግዚአብሔር ነቢዩ ሐጌንና ዘካርያስን አስነሥቶ ሕዝቡ እንደገና እንዲንቀሳቀሱ አደረገ። ከዚያም ሥራው እንዳይሰራ እንደኛው ከፍተኛ ችግር ምን እንደነበረ እግዚአብሔር ለዘካርያስ በልዩ ራዕይ አማካኝነት ነገረው።

(7). ዘካርያስ ምዕራፍ 3 አንብብ። በኢያሱ ላይ ክስ ለማቅረብ የቆመው ማን ነበር?

(8). ዘካ. 3:3ን እንደገና አንብብ። ሰይጣን ዘካርያስን የከሰሰበት ምክንያት ምን ነበር?

ዘካርያስ በኢያሱ ላይ ያየው የአደፈ ጨርቅ ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ የፈጸሙትን በደል የሚያመለክት ነበር። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር ለቀረበባቸው ክስ በዘካ 3:2 ላይ መልስ ሲሰጥ፦ "ሰይጣን ሆይ፥ እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገሥጽህ። በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ እይደለምን?" በማለት ተናግሮአል። በቁ. 4 እና 5 ላይ ደግሞ እድፋሙ ልብስ እንደወለቀለት ይናገራል። ከዚያም ኢያሱ የሚለብሰው ንጹህ የሆነ ልብስ ይሰጠዋል። የእግዚአብሔርን ሥልጣን የሚያመልክተውን ጥምጥሙን ሞሶር ይሰጠዋል። በቁ. 6-7 ላይ ኢያሱ ከጌታ ጋር በአዲስ ሕብረት እንዲመላለስ ከተነገረው በኋላ፥ በዚሁ ሕብረት ላይ የእግዚአብሔር በረከት እንዳረፈበት በዚሁ ምዕራፍ በመጨረሻው ቁጥር ላይ ይነግረናል።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሰይጣን እንዴት እድርጎ በእኛ ድካም ላይ እንደሚሠራ የሚያሳይ ነው። ድካማችን ላይ እንድናተኩር በማድረግ ይከሰናል። የእርሱም ክስ ራሳችንን እንድንጠራጠርና ተስፋ እንድንቆርጥ የሚያድርግ ነው። ብዙ ጊዜ እኛ አማኞች በቀላሉ ተስፋ እንቆርጣለን። እግዚአብሔር ግን እድፋሙን ልብስ እውልቆልን በፋንታው ንጹህ ልብስ እንዳለበሰን ማስተዋል አለብን። *የሰይጣንን ክስ ማድመጣችንን ባቆምን ጊዜ እግዚአብሔር ድካማችንንና ጥርጣሬአችንን ያስወግደዋል።* ሰይጣን አማኞችን በመክሰስ የሚፈጽመው ድርጊት "መፍረድ" ይባላል። መፍረድ ማለት፦ "እንድ ሰው ለአንድ ጉዳይ የማይበቃና የማይጠቅም እንደሆነ የሚወሰድል ሃሳብ ነው።" በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ኩነኔ እንደ ሌለባቸው በሮሜ 8:1 ላይ በግልጽ ይነግረናል። በዮሐ 3:18 ላይም "በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፣ በማያምን ግን በእንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል" በማለት ይነግረናል። ሰይጣን ሊፈርድብንና ድካማችንን ብቻ በማሳየት ከአሸናፊነታችን ሊያስቀረን ይሞክራል። እግዚአብሔር ግን እኛ ከፈቀድ ነለት፥ በመለኮታዊ ኃይሉ፥ እኛን ለውጦ ለሕይወታችን ያለውን ዓላማ ግቡ ለማድረስ ይችላል።

እግዚአብሔር ሰይጣንን ያሸነፈበት የመጨረሻ ድል በመጽሐፍ ቅዱስ በራዕይ 12:10-11 ላይ ሲገልጽ እንደዚህ ይላል፦

> አሁን የእምላካችን ማዳንና ኃይል፣ መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፣ ቀንና ሌሊትም በእምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሱት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።

(9). በራዕይ 12:11 ላይ ለአማኞች በሰይጣን ላይ ድል የሚሰጣቸውን ሦስት ነገሮች በእርሳስ ከሰራቸው በማስመር አመልክት።

እነዚህ ሦስት ድል መንሻ ኃይሎች ዛሬም ለእኛ የተሰጡን ናቸው። በ1ዮሐ 4:4 ላይ "ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" በማለት የተናገረውን ዘወትር ልናሰታውስ ይገባል።

በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሚገኝ ለውጥ

ዓላማ 6 በሐዋርያት ሥራ 17:6 ላይ አማኞች መንፈሳዊ ለውጥን እንዴት እንዳገኙ ለመግለጽ።

መጽሐፍ ቅዱስ የምንበረታታበት መጽሐፍ ነው። ብዙዎች እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው የመረጣቸው ሰዎች ልክ እንደ እኛ ነበሩ። ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ሕዝቅኤል፣ ጳውሎስ፣ ጢሞቴዎስና ሌሎችም እነርሱን የመሰሰሉት እንደኛው ድክመት የነበራቸው ሰዎች ቢሆኑም የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ውስጣቸው ገብቶ ለውጦአቸዋል። እንደዚህ ሰላለው ለውጥ በስፋት የሚነግረን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተስፋ ቆርጠው ተበታተኑ። ትንሣኤውም እንኳ ለእንዳንዶቹ መፍትሔ አልሆናቸውም ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ተስፋ እንደገባው መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ በወረደ ጊዜ ነገሮች ሁሉ ተለወጡ። እነርሱም በታላቅ ኃይል ተነሥተው ይሠሩና ይመለክሩ ጀመር።

(10). ዮሐ 14:26ን አንብብ። እግዚአብሔር አብ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ኢየሱስ በተናገረ ጊዜ፥ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ማን ብሎ ጠራው?

ሀ. ረዳት ለ. ፈዋሽ ሐ. ኃይል

ሐዋ. 1:8 ላይ ጌታ ኢየሱስ፣ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ተናገረ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተለወጡ ለምችን ታሪክ ያዘለ ነው። ሐዋርያቶች በዘመናዊ ትምህርት ያልሰለጠኑ፣ ተራ ሰዎች ነበሩ። እንደ ማንኛውም ሰው የራሳቸው የሆነ የግል ድካም የነበራቸው ለምችም ነበሩ። ሆኖም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል "ዓለምን የገለባበጡ ሰዎች" ነበሩ። መከራና መዓት በደረሰባቸው ጊዜ እንኳ ብርቱዎች ነበሩ።

(11). በሐዋ 17:6 ላይ "እነዚህ ዓለምን ያወኩ ደግሞ ወደዚህ መጡ" የተባሉት በመንፈስ ቅዱስ እየተረዱ ያሉ አማኞች ነበሩ። እነዚህ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መለወጣቸውን እንዴት ያሳይል?

እኛም ልክ እንደ እነርሱ መለኮታዊ ረዳት በሆነው ኃይል ለጌታ ኢየሱስ ምስክሮች መሆን እንችላለን። የክርስትና ሕይወታችን ዓላማና ግብ የት

ድረስ እንደሆነ ብናውቅም በራሳችን ኃይል እዚያ ለመድረስ የማንችል ደካሞች ነን። ደካሞች ስንሆን እግዚአብሔር በውስጣችን ኃይለኛ በመሆን በእግራችን እንድንቆም ያስችለናል። እግዚአብሔር እንድንፈፅመው ያዘዘንን ተግባር እንድናከናውን መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳናል። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ባሕርይ በእኛ ውስጥ እንዲሰርጽ ያደርጋል። ይህም ባሕርይ ክርስቶስን ወደ መምሰል ግብ ያስጉዘናል። ግቡም እውነተኛ የነርስቶስ ሙላት ወይም መንፈሳዊ ብስለት ነው።

የመከራ ፈተና

እጭር መልስ፡- ትክክለኛውን መልስ በተሰጠው ስፍራ ሙላ።

1. ሕይወታችንን እግዚአብሔር እንደሚያየው አድርገን መመልከት ጥቅሙ ምንድር ነው? _____

እውነት ሐሰት። መግለጫው እውነት ከሆነ 'እ' ሐሰት ከሆነ ደግሞ 'ሐ' የሚለውን ፊደል በክፍቱ ስፍራ በመጻፍ አመልክት፣

___ 2. አማኞች እግዚአብሔር ባደረገው ነገር ሊመኩ ይገባቸዋል።

____3. ሙሴ አፈ ትብ መሆኑን ለእግዚአብሔር አስታወቀ።

____4. መፍረድ ማለት አንድ ሰው ትክክልና የተከበረ መሆኑን መግለጽ ነው።

እዛምድ። በዚህ ክፍለ ትምህርት ትክክለኛ የሆኑ የትምህርቱን ሃሳብ የያዙ ምሳሌዎችን ታገኛለህ። በተራ ቁጥር 5-9 ያሉትን ምሳሌዎች ተስማሚ ከሆኑትና ከታች ከተሰጡት ሃሳቦች ጋር አዛምዳቸው።

5. ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱ የሆነ ድካም ነበረው፣ እግዚአብሔር እንዲያስ ወግዶው ከሚፈልገው፣ በሰውነቱ ላይ ካደረው ከሚያስቃየው ህመም ሆኖ በጣም ብርቱ የሆነ ክርስቲያን አገልጋይ ነበረ።

6. የሕዝቅኤል ስም በያዘው መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር 'ሙት ሰው' በማለት ሕዝቅኤልን ጠርቶታል።

7. እግዚአብሔር ሙሴ የሰጠውን ምክንያት በትዕግሥት አድምጦ፣ ያቀደለትን ዓላማ ሳያቋርጥ በተቃወመ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ።

8. ጢሞቴዎስ ማንም ታናሽነቱን ወይም ወጣትነቱን እንዳይንቀው የተመከረ ሰው ነበር።

9. አይሁዶች ከምርኮ ምድር ወደ አገራቸው በነፃነት በተመለሱበት ዘመን፣ ካህናቸው የነበረውን ኢያሱን ለመክሰስ ሰይጣን ተዘጋጅቶ ሲቆም፣ በዚያን ጊዜ ኢያሱ እድፋም ልብስ ለብሶ በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ ነበር።

_____ሀ. እግዚአብሔር ድካማችንን ያውቃል ሆኖም፣ ፈቃዱን በእርሱ ኃይል በእምነት እንድንፈጽም ይፈልጋል።

_____ለ. እግዚአብሔር በእርሱ ኃይል እንድንታመን የራሳችንን ሰብአዊነት ያሳስበናል።

_____ሐ. ሰይጣን ከአማኞች ድካም የተነሣ ወደ ፍርድ ሊያመጣቸው ይፈልጋል።

_____መ. አማኞች ያላቸው መንፈሳዊ ልምምድ ትንሽ ቢሆንም ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን አይከለክላቸውም።

_____ሠ. አማኙ ሲደክም የእግዚአብሔር ኃይል በውስጡ ይበረታል።

ምርጫ። የሚቀጥለው ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ስላለው ይህንኑ መልስ ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

10. ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ በአማኞች ላይ፡-

ሀ. ሐሰተኛ ሪፖርት ያቀርባል። ሐ. አባብ ይሆናል።
ለ. ክስ ያቀርባል። መ. ሐሰተኛ ነቢይ ይሆናል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. እግዚአብሔር የብርታት ምንጭ ሲሆን፥ የሰው ልጆች ደግሞ የድካም ምንጭ ናቸው።

7. ሰይጣን

2. ሀ

8. እድፋም ልብስ ለብሶ ነበር።

3. ጌታ ስላደረገው ነገር

9. 1. በበጉ ደም
   2. ከምስክራቸውም ቃል
   3. ሕይወታቸውን እስከ ሞት ድረስ ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆናቸው

4. ሐ

10. ሀ

5. ለ

11. ይህ አባባል የሚያሳየው እነዚህ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት መንፈሳዊ ለውጥን ያገኙ መሆናቸውን ነው።

6. ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ
ለ. መስበክ
ሐ. ማስተማር
መ. በውስጡ ያለውን መንፈሳዊ ስጦታ ቸል አለማለት።

የሙከራ ፈተና መልሶች

ክፍለ ትምህርት 1

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት

6. ሀ. ሙሉ እድገት
ሐ. ፍጹም የሆነ
መ. ሙሉ የሆነ
ሠ. የተፈጸመ

7. ሐ

8. ለ እና ሐ

9. ሰይጣን

10. እርጥበት የሌለው ድንጋያማ ስፍራ፣ እሾሃማ ስፍራ፣ ለምለም አፈር

ክፍለ ትምህርት 2

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት፥ የኢየሱስ ክርስቶስ

4. ሀ. መንፈሳዊ
ለ. አካላዊ
መ. አእምሮአዊ
ሸ. ማሕበራዊ

5. ሀ. ሥነ ምግባር የጎደለው
መ. አመንዝራነት
ሠ. ግብረ ሰዶም

6. ለ

7. ሀ. ቤተሰብ
ለ. ጓደኞች
ሐ. ባል ወይም ሚስት
መ. ጎረቤቶች

ክፍለ ትምህርት 3

1. ያደገ ወይም የበሰለ አማኝ ሲሆን

2. ሀ. 2
ለ. 4
ሐ. 3
መ. 1

3. ለ. ከሕግን
ሐ. ከእግዚአብሔር እርሻ
ረ. ከአፈር
ሸ. ከእግዚአብሔር ሕንፃ
በ. ከመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ

4. ሀ. ወርቅ
ሠ. ብር
ረ. የከበሩ ድንጋዮች

ክፍለ ትምህርት 4

1. ሐሰት፥ በአማኙ መንፈሳዊ ዕድገት ውስጥ ብዙ የሚያደርገው ነገር አለ።
2. እውነት
3. ሐሰት፥ ጠንካራ ምግብ ከሚወስደው ያነሰ በዝግታ ያድጋል።
4. ሐሰት፥ መንፈሱ ነው።
5. እውነት
6. ሀ
7. ከነዚህ ከዘጠኙ ውስጥ ማንኛውም አራቱ፦ ሰላም፣ ትዕግሥት ቸርነት፣ በጎነት፣ ፍቅር፣ ደስታ፣ ታማኝነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት

ክፍለ ትምህርት 5

1. ሐሰት፥ ወደ ተግባር እንድንቀሳቀስ የሚያደርገን ነው።
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት፥ ስራው (ሕይወቱ)
6. ዘ
7. ጊ
8. ጊ
9. ዘ
10. ዘ
11. ጊ
12. የክርስቶስ የፍርድ ወንበር

ክፍለ ትምህርት 6

1-7. የእንተ መልሶች
8. ሐሰት
9. ሐሰት
10. እውነት
11. ለ
12. አለማደግ፣ ጥብቅ የሆነ ሕብረት ማጣትና መንፈሳዊ በሽታዎች ሊሆኑ (ሌሎችም አሉ)።

ክፍለ ትምህርት 7

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. ንስሐ
9. በእግዚአብሔር ማመን
10. ጥምቀት
11. እጆችን መጫን
12. የሙታን ትንሣኤ
13. የዘላለም ፍርድ

ክፍለ ትምህርት 8

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. ሀ. በጎነት ሰ. ቸርነት ተ. የውሃት ኘ. ደስታ
   ሐ. ሰላም ሸ. እምነት ቸ. ራስን መግዛት
   ረ. ትዕግሥት በ. ታማኝነት ኀ. ፍቅር
7. የእንተ መልስ

ክፍለ ትምህርት 9

1. እውነት 2. ሐሰት 3. እውነት
4. የእድገት ሃሳብ
5. የእግዚአብሔርን መልዕክት መናገር
6. በአዲስ ቋንቋ መናገር
7. በአዲስ ቋንቋ የተነገረውን መተርጎም

8-10. ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ውስጥ ማንኛውም ሦስቱ ሊሆኑ ይችላሉ።
- የተራቡትን ማብላት።
- የተጠሙትን ማጠጣት።
- የታረዙትን ማልበስ።
- እንግዶችን መቀበል።
- የታመሙትን መጠየቅ።
- የታሰሩትን መጠየቅ።

ክፍለ ትምህርት 10

1. ሕይወታችንን እግዚአብሔር እንደሚያየው ካየነው እግዚአብሔር ወዳቀደልን ግብ ለመድረስ ያስችለናል።
2. እውነት
3. እውነት

4. ሐሰት፥ የማይበቃና የማይገባው እንደሆነ፣ ጥፋተኛ እንደሆነ የሚያሳየው

5-9. ሀ. 7 መ. 6
   ሰ. 6 ሠ. 5
   ሐ. 9
10. ለ